

እምነት ካላችሁ እባቡንና ጊንጡን ብትረግጡት አይጐዳችሁም የሚለው አምላካዊ ቃል የተፈጸመላቸው ታላቁ ጻድቅ አቡነ አረጋዊ ዘደብረ ዳሞ

ዋጋ 2

... ማተሚያ ቤት ታተመ

# « ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ »



ዐረገ ውስተ አርያም ... ጸጋሁ ለኲሉ እንስ እመሕያው

- ጻድቁ አቡነ አረጋዊ ፀበል ከሰው ሆድ እባብ አውሬ ወጣ
- የማይናገሩት ባሕታዊ
- የጋሥጫ አባ ጊዮርጊስ ገድም ታሪክ

ቍጥር ፲፰, ፲፱፻፹፰ ዓ.ም
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት፡ታሪክና ባሕል፡የመንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ዜና ለሕዝበ ክርስቲያን የሚያቀርብ» ስለሆነ «ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶ ዶክስ» ተብሎ ተሠይሟል ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ኮሚቴ እየተዘጋጀ በየወሩ አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

ዋና አዘጋጅ ሊቀ ልሳናት ነቅዐ ጥበብ ወንድም
ረዳት አዘጋጅ መ/ ኤፍሬም በየነ

ስልክ 11 26 63
የመልእክት ሣጥን ቍጥር 1283
አዲስ አበባ

# « ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ »

ቍጥር ፲፰, ፲፱፻፹፰ ዓ/ም
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

## ማ ው ጫ


| ተ. ቁ. | | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | ርእሰ አንቀጽ | ፭ |
| ፪ | ቅዱስ ፓትርያርኩ በምግብ ለሥራ የተሠሩ መንገዶችን መርቀው ከፈቱ | ፮ |
| ፫ | የቅዱስ ጊዮርጊስ ተጋድሎ | ፯ |
| ፬ | ቅዱስ ማርቆስ | ፰ |
| ፭ | በአቡነ አረጋዊ ፀበል ከሰው ሆድ አውሬ ወጣ | ፱ |
| ፮ | የማይናገሩት ባሕታዊ | ፲፪ |
| ፯ | የጋሥጫ አባ ጊዮርጊስ ገዳም ታሪክ | ፲፫ |
| ፰ | በዐለ ዕርገት | ፲፭ |
| ፱ | ርክበ ካህናት | ፲፮ |
| ፲ | ድንግል ማርያም በደብረ ምጥማቅ | ፲፰ |
| ፲፩ | ጰራቅሊጦስ | ፲፱ |
| ፲፪ | እባብ ተሸክመው የኖሩት ሴት | ፳፩ |
| ፲፫ | ቅ/ፓትርያርኩ በአርሲ ሀገረ ስብከት የልማት ሥራዎችን ጐበኙ | ፳፪ |
| ፲፬ | የሴቶች ምሥክርነት | ፳፭ |
| ፲፭ | ልደታ ለማርያም | ፳፮ |
| ፲፮ | ስብረተ አጽሙ ለተክለ ሃይማኖት | ፳፯ |




ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org

ርእሰ አንቀጽ

# ከፅንስ እስከ ዕርገት

የጌታችን የመድኃኒታችን የወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን በምድር ላይ መመላለሱን ዕውር ማብራቱን ሕሙሙ መፈወሱን በኋላም በሠላሣ ዘመኑ መጠመቁን ስቅለቱን ሞቱን ትንሣኤውን ማረጉንና ዳግም ምጽአቱን በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ቅዱሳ አበው ነቢያት በመንፈስ ቅዱስ ተናግረውት ነበር ።

ከቅድሳን ነቢያት በተነገረው ትንቢት በተቆጠረው ሱባኤ መሠረት ጊዜው ሲደርስ እግዚአብሔር ወልድ በብሥራተ መልአክ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በየጥቂቱ አደገ በዚህም ዓለም ዞረ አስተማረ በኋላም ’’ ነሥአ ደዌነ ወጾረ ሕማመነ ’’ኢሳ ፶፫ / ፩-፲፪

’’ በእውነት ደዌያችን ተቀበለ ሕማማችንም ተሸከመ - - - እርሱ ስለመተላለፋችን ቆሰለ ስለ በደላችንም ደቀቀ የድህነታችንንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ አኖረ ’’ ተብሎ በነቢዩ በኢሳይያስ እንደ ተነገረው በአመፀኞች በአይሁድ እጅ ተይዞ ያለምንም በደል ተላልፎ ለሞት ተሰጠ በመስቀል ላይም ተሰቅሎ ሞተ ።

አስቀድሞ ነቢዩ ዳዊት ይትነሣእ እግዚአብሔር ወይዘረው ጸሩ ወይጐየዩ ጸላዕቱ እምቅድመ ገጹ ወከመ የሐልቅ ጢስ ከማሁ የሐልቁ መዝ ፷፯ ቁ ፩-፯ እግዚአብሔር ይነሣ ጠላቶችም ይበተኑ የሚጠሉትም ከፊቱ ይሽሹ ጢስ እንደሚበን እንዲሁም ይብነኑ በማለት በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ ፣ እንደተናገረውና እንደዘመረው ራሱ ባለቤቱ ጌታም ወበከመ ሐደረ ዮናስ ውስተ ከርሠ አንበሪ ሠሉሰ መዋዕለ ወሰሉሠ ለያልየ ከማሁ ሐለዎ ለወልደ እጓለመሕያው ይሕድር ውስተ ከርሠ ምድር ።

ዮናስ በከርሠ አንበሪ ሦሥት ቀንና ሦሥት ሌሊት እንዳደረ እንዲሁም የሰው ልጅ በከርሠ ምድር በመቃብር ሦሥት መዓልትና ሦስት ሌሊት አድሮ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ይነሣል በማለት ጌታ ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት ስለ ትንሳኤው ለደቀ መዛሙርቱ በተናገረው መሠረት በሞተ በ፫ኛው ቀን መቃብር ከፈቱልኝ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል በሞቱ ሞትን ደምስሶ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቷል ።

ከሙታን ተለይቶ ከተነሣም በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ ኤማሁስበተባለ ጉዳና በባሕር ፣ አጠገብ በተዘጋ ቤት እየተገለጸ እስከ አርባ ቀን ድረስ ነገረ ትንሣኤውን ከአስተማራቸው በኋላ አስ ቀድሞ በነቢዩ ዳዊት ” ዐረገ እግዚአብሔር በይባቤ ወእግዚእነ በቃለ ቀርን ዘምሩ ለአምላክነ ዘምሩ ”፣ ተብሎ እንደተጻፈው ከሙታን ተለይቶ በተነሣ በ፵ ቀን በይባቤ መላዕክት በዝማሬ መላዕክት ወደ ሰማይ ዐርጓል በአባቱም ቀኝ ተቀምጦ አል የሐዋ ሥራ ፩ ፣ ፱-፲፩

እንግዲህ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ነገረ መስቀል የተፈጸመው ከፅንስ እስከ ዕርገት ባለው ጊዜ ነው ይህም ማለት የሰው ልጅ በደል በይቅርታ ኃጢአቱ በጽድቅ ውርደቱ በክብር ሞቱ በሕይወት የተተካበት እንዲሁም ’’ ሣህል ወርትዕ ተራከባ ጽድቅ ወሰላም ተሰአማ ርትዕሰ እምድር ሠረጸት ወጽ ድቅኒ እምሰማይ ሐወጸት ’’ መዝ ፹፬ ፲-፲፩

ምህረትና እውነት ተገናኙ ጽድቅና ሰላም ተስማሙ እውነት ከምድር በቀለች ጽድቅ ከሰማይ ተመለሰች በማለት ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ የተናገረው የተስፋ ቃል የተጠናቀቀው በዚሁ ከጽንስ እስከ ዕርገት ባለው የጌታ መዋዕለ ሥጋዌ መሆኑን ከላይ በተዘረዘሩት የቅዱሳት መጻ ሕፍት ዐረፍተ ንባብ ልንገነዘብ እንችላለን ።

መሪጌታ ኤፍሬም በየነ

www.ethiopianorthodox.org

# ቅ/ፓትርያርኩ በምግብ ለሥራ የተሠሩትን መንገዶች መርቀው ከፈቱ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በክልል ፫ በደቡብ ወሎ መስተዳደር ከቢሲትማ እስከ ሐይቅ ገዳምና ከቦሩ ሜዳ ሆስፒታል እስከ ቦሩ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በምግብ ለሥራ የተሠሩትን መንገዶች ሚያዝያ ፲፩ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ/ም መርቀው ከፍተዋል ።

መንገዶቹ የተሠሩት በደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት አሳሳቢነትና ጥረት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮምሽን የምግብ ለሥራ ፕሮግራም ሲሆን ከቦሩ



ቅዱስነታቸው በምግብ ለሥራ የተሠሩ መንገዶችን መርቀው ሲከፍቱ

ሜዳ እስከ ቦሩ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የተሠራው ፰ ኪሎ ሜትር መንገድ ብር 147240 (አንድ መቶ አርባ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ አርባ ብር) የፈጀ ሲሆን ከቢስቲማ እስከ ሐይቅ ገዳም ድረስ የተሠራው ፯ ኪሎ ሜትር መንገድ ብር 94220 (ዘጠና አራት ሺህ ሁለት መቶ ሃያ ብር) የፈጀ መሆኑ ታውቋል ።

ቅዱስነታቸው መንገዶቹን መርቀው ከከፈቱ በኋላ በሰጡት ቃለ ቡራኬ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሲጀመር ጀምሮ ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ በሁለንተናዊ መልኩ የሕይወት ገዳና ሆና የኖረች መሆኗን ጠቅሰው ከሥልጣኔ አንዱ የመገናኛ መንገድ መሥራት ስለሆነ መገናኛ ከሌለም ከአንዱ ክፍል የሚገኘው ጥቅም በሌላው ክፍል ሊገኝ ስለማይችል ሀገረ ስብከቱና የአካባቢው ሕዝቦች ይህን ችግር ተረድተው መንገዶቹ ተሠርተው ለሕዝብ ጥቅም እንዲሰጡ በማድረጋቸው አመስግነዋቸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በዚሁ ዕለት ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ በግል ገንዘባቸው በሐይቅ ገዳም በብር 130,000 (አንድ መቶ ሰላሳ ሺህ ብር) ያሰሩትን ባለ ፮ ክፍል የሊቀ ጳጳስ መኖሪያ ቤትና በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ርዳታ በብር 15000 (አስራ አምስት ሺህ ብር) የተሠራውን 12 ክፍል የመነኮሳት መኖሪያ ቤት መርቀው ከፍተዋል ።

ቅዱስነታቸው በዚህ አጋጣሚ በኮምቦልቻ በደሴ ከተማና በአካባቢዋ በሚገኙት አብያተ ክርስቲያናትና እንዲሁም በታሪካዊው የቦሩ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተዘዋውረው ለምዕመናን ቃለ ምዕዳን አሰምተዋል ።

## የቅዱስ ጊዮርጊስ ተጋድሎ

ተጋድሎ ማለት ስለ ሃይማኖት ሲያስተምሩ በአላውያን መንግሥታት ፣ ስለዕውነት ሲመሰክሩ በሐሰተኞች መሰቃየት ፣ ወንጌልን ሲያስተምሩ በከሃዲያን እጅ መሞትና እነዚህንም የመሳሰሉት ናቸው ። ስለነዚህ ነገሮች ብዙ ቅ/ሰማዕታት ሕይወታቸውን አሳልፈዋል ፣ የታሰሩ የተገረፉ ፣ በሰይፍ የተቆረጡ ፣ በእሳት የተቃጠሉና በተለያዩ ሥቃያት የተፈተኑ ብዙዎች ናቸው ።

ከነዚህም አንደኛው ሊቀ ሰማዕታት ቅዱስ ጊዮርጊስ ነው ። የቅዱስ ጊዮርጊስ አባት ዘሮንቶስ (አንስጣስዮስ) ይባላል ። የተወለደውም ፋርስ በሚባለው (መካከለኛው ምሥራቅ) ቀጰዶቅያ በምትባል ቦታ ነው ። የእናቱም ስም ቴዎብስታ ሲሆን አገሩዋ በፍልስጥኤም ውስጥ ልዳ በምትባል አገር ነው ። ቅ/ጊዮርጊስ በእነዚህም አገሮች እየተዘዋወረ የወንጌልን ብርሃን በማዳረሱ «ፀሐየ ልዳ ኮከበ ፋርስ» ተብሏል ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ በልጅነቱ አባቱ ስለሞተ በዘመኑ ወደነበረው ንጉሥ ዱድያኖስ ሄደ ። ይህም ንጉሥ ብልህነቱንና አስተዋይነቱን አይቶ የአንድ ክፍለ ጦር አዛዥ አድርጎ ሾመው እሱም በሄደበት ቦታ ሁሉ በእምነትና በጀግንነት እየተዋጋ ብዙ ድልን በማስገኘቱ በየሀገሩ ዝናው የታወቀ ሆነ ።

በዚህም ዘመን አምልኮተ ጣኦት የተስፋፋበት ፣ ክርስቲያኖች የሚሰቃዩበት ወቅት ነበር ። ንጉሡ ዱድያኖስም ታላላቅ የጣኦት ቤቶችን አሠርቶ በውስጡ ሰው ሠራሽ አማልክትን በማስቀመጥ የሚያመልከውና የሚሰግደው ለነሱ ነበር ።




ገድለኛው የሰማዕታት አለቃ ቅዱስ ጊዮርጊስ

ቅዱስ ጊዮርጊስ አምልኮተ ጣዖትን እየተቃወመ ፣ ሰማይና ምድርን የፈጠረ የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ አንድ አምላክ እንደሆነና ያለእርሱም ሌላ አምላክ እንደሌለ ፣ አምልኮትና ስግደትም የሚገባው ለእርሱ ብቻ መሆኑን እያስተማረ ብዙዎችን ወደክርስትና እምነት ስለመለሰ ንጉሡ ተቆጥቶ ከዚህ አድራጎቱ ተመልሶ እሱ ለሚሰግድለት ጣኦት እንዲሰግድ ቢጠይቀው የማይመለስለት በመሆኑ «ሹመት እጨምርልሃለሁ ልጄንም እድርልሃለሁ» በማለት ወደቤተ መንግሥቱ እንዲገባና እንዲመክር አደረገ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስም ወደ ቤተ መንግሥት መግባት ለወንጌል ትምህርቱ አመች ሆኖ ለት የንጉሡን ቤተሰብና ሠራዊት ስለክርስቶስ ማስተማሩን ቀጠለ ብዙዎችንም አሳመነ ፣ ይልቁንም የንጉሡን ሚስት አሳምኖና አጥምቆ እስከመጨረሻው ድረስ በክርስትና እምነት ጸንታ በሰማዕትነት ሕይወቷን እንዳሳለፈች ገድሉ ያብራራል ።

ንጉሡ ዱድያኖስም እጅግ ተቆጥቶ ሰብአ የፋርስ ነገሥታትን ሰብስቦ በቅዱስ ጊዮርጊስ ላይ ምን ዓይነት ቅጣት እንደሚወሰኑ ጠየቃቸው ። እነዚህም ነገሥታት ቅዱስ ጊዮርጊስን ጠርተው ፈጣሪውን እንዲክድ ለጣኦታቸው እንዲሰግድ ጠየቁት ። እርሱ ግን ሳይፈራና ሳያፍር ዕውነተኛው አምላክ ፈጣሬ ሰማያት ወምድር መሆኑንና ጣኦታት የሰው እጅ ሥራ በመሆናቸው የማይሰሙ ፣ የማይለሙ የአጋንንት ማደሪያ እንደሆኑ በመዘርዘር አስረዳቸው ።

እነሱ ግን ማመን ስለተሳናቸው ምልክት እንዲያሳያቸው ጠየቁት እሱም ወደፈጣሪው በመጸለይ ሰባው ነገሥታት የተቀመጡባቸውን ሰብዓ ፣ ወምበሮች አለምልሞ አሳይቷቸዋል በዚህም ማመናቸው ቀርቶ እንዲያውም በዚህ ታምራቱ ሕዝቡን እየሳበ ወደ ክርስትና እምነት የሚመልስ ፣ ጣኦቶቻቸውን የሚያረክስ ፣ ክብራቸውን የሚያዋርድ መስሎ ስለታያቸው በሰይፍ ተቆራርጦ በእሳት ተቃጥሎ አመድ ሲሆን በነፋስ እንዲበተን አድርገውታል ።

ነገር ግን የእግዚአብሔር ኃይልና ረቂቅ መንፈስ (ሥራው) ከእርሱ ስላልተለየ እንደገና በመነሣት ብዙ አሕዛብን አስተምሮ አሳምኖ ወደ ክርስትና መልሷል ። ከእርሱም ጋር የነበሩ ተከታዮች ሰማዕታት እንደእሱው ወንጌልን አስተምረው ፣ አጥምቀው ስለክርስቶስ መስክረው በሰማዕትነት አርፈዋል አስቀድሞ ነቢዩ« ስለአንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን ፣ እንደሚታረዱ በጎችም ተቆጠርን» ሲል የተናገረውን ፈጽሟል ።

ቅዱስ ጊዮርጊስም ተጋድሎውን በመቀጠል በየጊዜው ያልደረሰበት ሥቃይ የለም ። መርዝ አጠጡት ፣ በሰንሰለት አሥረው መሬት ለመሬት ጎተቱት ፣ እንደሀል በአውድማ አድርገው በከብት አበራዩት ፣ እንደእንጨት በመጋዝ ሰነጠቁት ፣ በ[illegible]ተር ፈጩት ፣ ይህ ሁሉ ሲፈጸምበት ፍርሃትና ጥርጣሬ አላደረበትም ። እንደበቱም ስለክርስቶስ ከመመስከር ወንጌል ከማስተማር አላቋረጠም ። «ስለዚህ ስለ ክርስቶስ በድካም ፣ በመንገላታትም በስደትም ፣ በጭንቀትም ደስ ይለኛል ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝና» ሲል ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ቅ/ጊዮርጊስ በእነዚህ ሁሉ በረታ እንጂ አልደከመም ።

ሰባት ዓመት ሙሉ በዚህ ዓይነት ሲጋደል ከቆየ በኋላ ወደፈጣሪው በመጸለይ በስሙ የተማጸነ ፣ መታሰቢያውን ያደረገ ፣ ቤተ ክርስቲያኑን ያሳነፀ በስሙ መልካም ሥራ የሠራ ሁሉ ቢቸገር እረዳዋለሁ ፣ ቢታመም እፈውሰዋለሁ ፣ በመከራው ሁሉ እደርስለታለሁ ኃጢአቱንም እደመስስለታለሁ «የሚል ቃል ኪዳን ተቀብሎ» የጻድቃን ሞታቸው እረፍታቸው ነውና አንገቱን ተሰይፎ ሚያዝያ ፳፫ ቀን አርፏል ። በዚህም ጊዜ የ፯ ዓመቱን ተጋድሎ የሚመሰክሩ ፫ አክሊላት ወርደውለታል ። አንገቱን በቆረጡት ጊዜ ደም ውሃና ወተት ፈሷል ። ስለዚህ

www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ክርስቲያኑ በታነጸበት ጽላቱ ባለበት ሁሉ በየ ዓመቱ በዓሉ በታላቅ ድምቀት ይከበራል ።

ወርቅ በእሳት ተፈትኖ ጥራቱ እንደሚታወቅና ክፍ ያለ ዋጋ እንደሚያወጣ ሰማእታትም በእሳትና በስለት ተፈትነው እውነተኛ የክርስቶስ ተከታዮች በመሆን ብዙ ተከታዮችንም አፍርተው ፣ አሰበ ተጋድሎአቸውን አግኝተው አልፈዋል ። እውነተኛ ክርስቲያኖችም የእግዚአብሔር ወዳጆች የሰማዕታት ተከታዮች መሆናቸው የሚታወቀው በየጊዜው የሚ ደርሱባቸውን ፈተናዎችና ችግሮች በትእግሥት ተቀ ብለው የነርሱንም አርአያነት (በመከተል) ለትው ልድ ሲያስተላልፉ ነው ።

መ/መንክር ዋሴ

# ወንጌላዊው ቅ/ ማርቆስ

ጌታው ሲያዝ ልብሱን ትቶ ራቁቱን ሸሸ/ማር ፲፬-፶፩/ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም እየተመላለሰ ያስተምርበት በነበረው ጊዜ በግምት የአምስት ገቢያ የሚያህሉ ሰዎች እየ ተከተሉ ትምህርቱን ያዳምጡት ነበር ዓላማቸው ግን የሁሉም የተለያየ ነበር አንዳንዱ የወንጌልን መብለጥ የኦሪትን ማነስ አነጻጽረው የበለጠውን ለመከተል ሲሆን ሌሎች ደግሞ ነቢዩ ዳዊት «ይሜኒ ላህዩ እምውሉደ እጓለ እመ ሕያው » መልኩ ደም ግባቱ ከሰው ልጆች ይልቅ ያምራል መዝ - ፵፬ -፪ ተብሎ የተነገረውን መሠረት በማድረግ መልኩን ለማየት ነበር የተራቡት የተጠሙት የታረዙት ያበላ ናል ያጠጣናል ያለብሰናል ፣ እያሉ በተስፋ ሲከተሉት የታመሙትም እንዲያድናቸው ይከተሉት ነበር እን ዲሁም ንጉሡን ቄሣርን የተሳደበ እንደሆነ ተናግ ረን እናጣላዋለን በማለትም የሚከተሉት ነበሩ ።

የተለያየ አስተሳሰብ ከነበራቸው ሕዝቦች ጋር አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ሰባ ሁለት አርድዕት ሰላሳ ስድስት ቅዱሳት አንስት ነበሩ መቶ ሃያ ቤተሰቦች የሚባሉትም እነዚህ ናቸው እነዚህ ቀን ከሕዝቡ ጋር ሲማሩ እየዋሉ ሌሊትም ካደረበት ያድራሉ ፤ ወንጌልንም በዕጣ ተከፋፍለው በሙላው ዓለም እን ዲዳረስ ያደረጉት እነርሱ ናቸው «ድምጻቸው ወደ ምድር ሁሉ ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ ደረሰ እንዲል መዝ ፲፰-፬)

ከሰባ አርድዕት አንዱ ወንጌላዊው ማርቆስ ነው ፣ የዚህ ሐዋርያ አባቱ አርስጣቡሎስ የሚል ሥያሜ ሲኖረው እናቱ ማርያም ትባላለች ቁጥሯ ከሰላሳ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት ነው ልጅዋን ማር ቆስን በተለያዩ ቋንቋዎች ለመናገር እንዲችል በሕ ፃንነቱ እንዲማር አድርጋዋለች ፣ ቤቷን ለስብከተ ወንጌል መዘጋጃ ስለሰጠች ሐዋርያት እየተሰበሰቡ የሚጸልዩ ትና ስለስብከተ ወንጌል የሚመካከሩትም በማርቆስ እናት በማርያም ቤት ነበር ፣ የማርቆስ የመጀመሪያ ስሙ ዮሐንስ ነበር ወንጌላዊው ማር ቆስ ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር እየሄደ የማስተማር ስል ትን በሚገባ አጥንቶ ነበርና ብቻውን ለማስተማር ወደ ግብጽ ሄዶ እስክንድርያ ከተማ ለመግባት ከበሩ ሲደርስ የጫማው ማዘቢያ ተበጠሰበት ከአጠገቡ አንድ ጫማ ሰፊ ስለተመለከተ ቀረብ አለና የተቆ ረጠውን ጫማውን እንዲሰፋለት ጠየቀው ።

ጫማ ሰፊውም እሺ ብሎ ጫማውን ተቀብሎ ሲሰፋ ተሳስቶ በሚሰፋበት ወስፌ ጣቱን ሲወጋው በዩናናውያን ቋንቋ «ኢስታኦስ» አለ ትርጓሜው አንድ እግዚአብሔር ማለት ነው ሐዋርያው ማር ቆስ የእግዚአብሔርን ስም በመጥራቱ ደስ ስላለው ፈገግ አለና አሁን የጠራሃውን ታውቀዋለህን አለው ትርጓሜውን አላውቀውም ነገር ግን ቃሉ ለሀገራ ችን ዕንግዳ አይደለም እኔ ብቻ ሳልሆን ሁሉም ይና ገረዋል አለው ወዲያው የቃሉን ትርጓሜ በሚገባ አስረዳው ፣ ጫማ ሰፊው በአነጋገሩ ስለተደሰተ ወደቤቱ ሄዶ እንዲጋበዝለት ለመነው ፣

ወንጌላዊው ማርቆስ ወደ ቤቱ ሂዶ ከተጋበዙ በኋላ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከጽንስ ጀምሮ እስከ ዕርገት ያደረገውን ተአምር ስለአስተማራቸው ያ ጫማ ሰፊና ቤተሰቦቹ በእግ ዚአብሔር ስም አመኑ ወንጌላዊውም በአብ በወ ልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠመቃቸው ፣ የጫማ ሰፊው ስምም አናንያኖስ ነው ይህንኑ ሰው ኤጲስ ቆጶስ አድርጎ ሹሞላቸው ለማስተማር ወደ ሌላ ሀገር ሂዷል ።

ሐዋርያው ማርቆስ ጠንክሮ በማስተማር ሕዝ ቡን ከአምልኮ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ስለመለሳቸው ፣ የጣዖታት ማምለኪያዎች የነበ ሩት ቤቶች ባዷቸውን ሲቀሩ ጣዖታቱም እየተሰባ በሩ ወድቀዋል ፣ ስለዚህ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በድ ርሰቱ «በግብጽ ጣዖት የሚመለክባቸውንና ጣዖ ታቱን ሰባብሮ በመጣል አምልኮ ባዕድን ያጠፋ ማር ቆስ እንደ አንበሳ ነው ሲል ተናግሯል ።

ወንጌላዊው ማርቆስ ከገድሉ ጽናት የተነሣ የዕውራንን ዓይን አብርቷል የለምጽ በሽታ የያዛ ቸውን አንፅቷል ሽባዎችን አንካሶችን ፈውሷል ፣ በእግዚአብሔር ኃይል በሚያደርጋቸውም ተአም ራት ዓረማውያን በጣም ቀንተው ሊገድሉት እስ በጡ የሚያገኙበትን መንገድ ይፈልጉ ጀመር ሚያ ዝያ ፳፱ ቀን ከቤተ መቅደስ ገብቶ ሲቀድስ ዓረማ ውያን በውጭ ቆመው ይጠብቁት ነበር ወደውጭ ሲወጣ በገመድ አሥረው በእስክንድርያ ከተማ እየ ጎተቱ አዞሩት ሥጋው በየዕንጨቱ በየድንጊያው ተቆራረጠ ደሙም በመሬት ላይ ተንጣለለ (ፈሰሰ) ቅዱስ ማርቆስ መከራውን አልተሰቀቀውም እንዲያውም በክርስቶስ ስም አምኖ ስለደረሰበት ሥቃይ እግዚአብሔርን አመሰገነ ።

ዓላውያን አሥረው ከተማ ለከተማ ከጎተቱት በኋላ ከአሥር ቤት አስገብተው ጠባቂዎችን አቆሙ ጠባቂዎች ተኝተው ሳሉ ታላቅ ንውጽውጽታ ሆነ የእግዚአብሔር መልአክ ከሰማይ ወርዶ የቅዱስ ማርቆስን ሥጋ ዳሰሰና አንተ ሊቅ ነህ ሁሉን በትም ህርትህ የምታጽናና እነሆ ስምህ በሕይወት መጽ ሐፍ ተጽፎአል ከሐዋርያትም ጋር ተቆጥረሃል ፣ እግዚአብሔር አምላክ ጸጋንና ኃይልን ስለሰጠህ ሥጋህ በምድር አይጠፋም ነፍስህም በመንግሥተ ሰማያት በደስታ ትኖራለች አለው ቅዱስ ማርቆስ ይህንን አስደሳች ቃል በሰማ ጊዜ እጁን ወደ ሰማይ ዘርግቶ ፣ አቤቱ አምላኪየ ፈጣሪዬ ሆይ ! ከፊትህ አልጣልከኝምና አመሰግንሃለሁ በሰላም ነፍሴን ተቀ በላት ብሎ ሲጸልይ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስ ተገልጾ ሰላሜ ከአንተ ጋር ይሁን ብሎ ቃል ኪዳን ከሰጠው በኋላ ወደሰማይ ዓረገ ሐዋርያው ቅዱስ ማርቆስም ወዲያው አረፈ ።

ዓረማውያን እንደሞተ ባዩ ጊዜ ሥጋውን ለማ ቃጠል እሳት አነደዱ ፣ ወዲያው በእግዚአብሔር ፈቃድ ጨለማ ጭጋግ ነፋስ ውርጭ ሆነ ፀሐይ ጨለ መ መብረቅ ነጎድጓድ ዝናም ሆነ እሳቱም ጠፋ አላ ቃጠለውም በዚያው ሀገር ከሚኖሩ መኳንንት መሳ ፍንት ፣ ሽማግሌዎች ሊቃውንት ብዙዎቹ ሞቱ ፤ ደጋግ ሰዎች ግን መጥተው የቅዱስ ማርቆስን ሥጋ ገንዘው በዝማሬ በውዳሴ በቅዳሴ ወስደው በተቀደሰ ቦታ አስቀመጡት ።

የቅዱስ ማርቆስ ዕረፍቱ ሚያዝያ ፴ ቀን ስለ ሆነ በስሙ በታነጹ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ዕለቱ ተከብሮ ይውላል ፣ በዚሁ ዕለት ጧፍና ዕጣን ገዝቶ ግርር ሰፍሮ ሌሎችንም ንዋያተ ቅድሳት ገዝቶ ስለ አምላከ ማርቆስ ብሎ ያቀረበ እንዲሁም ቢቻለው ዳቦ ጋግሮ ጠላ ጠምቆ ቆሎ ቆልቶ ፣ ባይቻለው ቀዝ ቃዛ ውኃ ቀድቶ ለተጠሙ ነዳያን ያጠጣ በምድር ሀብተ ሥጋን ፣ በረከተ ሥጋን ያገኛል በወዲያው ዓለምም የማታልፍ መንግሥተ ሰማያትን ወርሶ በተድላ በደስታ ይኖራል ።

ስለዚህ እኛም በእግዚአብሔር ስም አምነን በሐዋርያው ማርቆስ በመማጸን የተራበ አብልተን የተጠማ አጠጥተን የታረዘ አልብሰን የእግዚአብሔ ርን መንግሥት ለመውረስ ያብቃን ።

«ቂስ ሊቀ ኅሩያን ልሣኑ በዛብኅ

# በአቡነ አረጋዊ ጸበል ከሰው ሆድ አውሬ ወጣ

«እምነት ካላችሁ እባቡንና ጊንጡን ብትረግጡ አይጐዳችሁም በጠላትም ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻ ችኋለሁ» የሚለው የእግዚአብሔር ቃል በጽኑ እምነታቸው ተፈጽሞላቸው ሰው የሚአጠፋ ውና የሚውጠው ዘንዶ ለማዳ እንስሳ (ፈረስ) ሁኖ ላቸው ታላቁን የዳሞ ተራራ በዘንዶው ጅራት የወ ጡት ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ ታላቁ ጻድቅ አባታ ችን አቡነ አረጋዊ ናቸው ።

በ፭ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ወደ ሀገራችን የገ ቡት ጻድቁ አባታችን አቡነ አረጋዊ በገድላቸው ጽናት በትሩፋታቸው ብዛት በሀገራችን በኢትዮጵያ የታወቁና የተወደዱ ናቸው ።



ታላቁ ጻድቅ አቡነ አረጋዊ ዘደብረ ዳሞ

ጻድቁ አባታችን አቡነ አረጋዊ በኢትዮጵያ ለነበሩትና ለሚኖሩት ቅዱሳን ሁሉ በቅድስና በድ ንግልና ጸንተው ለሚቀበሉት አስኬማ መላእክት የቆብ አባት ናቸው ፤ በጻድቁ አባታችን ስምበታነጹት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በስማቸው የፈለቀው ፀበል በሽተኞችን እየፈወሰ ነው ፤ እጅግ አስደናቂ የሆኑ ተአምራትም በየጊዜው ይፈጸማሉ ።

በቅርቡ በአዲስ አበባ የደብረ ከዋክብት አቡነ አረጋዊና ገብረ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባዔ ጽ ቤት እንደተገለጸው ወሮ ብዙ አየሁ ጌታቸው የተባሉ ከጊዜ በኋላ በአደረባቸው ሕመም ምክንያት ፈውስ ለማግኘት ሠይጣን በሚ መለክበት በየቃልቻው ቤት በየጠንቋዩ ፡ በየጫት ቃሚውና በየአውሊያው ቤት እስከሚታክታቸው ድረስ ቢመላለሱም በደዌ ላይ ደዌ ከመጨመር በስተቀር አንድም ፈውስ ሊአገኙ አልቻሉም ነበር ።

በኋላ ግን በሽተኛ ሁነው ሲኖሩ ከብዙ ዓመ ታት በኋላ የአዲስ አበባ ደብረ ከዋክብት አቡነ አረጋዊን ጸበል ጠጥተው ከሰው ሆድ ወጣ ብሎ ለማመን የሚአስቸግር አውሬ እንደወጣላቸውና ይህም አስገራሚ አውሬ ለሀኪሞች ቀርቦ መታ የቱንና በኢትዮጵያ ራዲዮና ጋዜጣ የተገለጸ መሆ ኑን ወደ ጽ/ቤታችን የተላለፈው ደብዳቤ ያስረዳል ። የተፈወሱት ሴት ለደብሩ ጽ/ቤት የሆኑትና የተና ገሩትን ከብዙ በጥቂቱ ከዚህ ቀጥሎ አቅርበነዋል ።

ጥቅምት ፲፩ ለጥቅምት ፲፪ አጥቢያ በህልሜ ቀይ ሴት ነጭ በነጭ ለብሳ ከሆድሽ ያለውን ነገር ሃኪም ስለማያገኘው እኔ ላውጣልሽና ወደ ልጆችሽ



www.ethiopianorthodox.org

ተመለሽ ብላ እንዴት እንደወጣ ሳላውቅ አንድ የሆነ ነገር ይዛ ወደ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ላይ ጥላ አድኝሻለሁ ከአሁን በኋላ አያምሽም ትለኝና እባ ንናለሁ ከዛ ሲነጋ ለእናቴ ነገርኳትና እናቴም ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዳ በትንሽ ብልቃጥ ጸበል ይዛ ልኝ መጥታ አጠጣችኝ ቀኑን ሙሉ ሰላም ውየ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ሲሆን ምን እንደሆን የማይ ታወቅ ትልቅ ጥቁር ጸጉር ያለው አውሬ ከማህጸኔ ወጣልኝ እኔም በጣም ደንግጬ እናቴን ጠራኋትና ምንድን ነው ይኸ አውሬ ብዬ ሳሳያት ከንጹህ ውሀ ላይ አድርጋ ስታየው ነፍስ የለውም ጎሽ እመብርሃን ገላገልችሽ ይኸ ነው በሽታሽ ከአሁን በኋላ



በአቡነ አረጋዊ ፀበል ከሆዳቸው አውሬ የወጣላቸው ወ/ሮ ብዙአየሁ ጌታቸው

አትታመሚም አለችኝ እኔም በጣም እየተሻለኝ መጣ እንደዚያው እየተጠናከርኩኝ እንዳለ አልፎ አልፎ ቃርና ትውከት ያመኝ ነበር በዚህ ጊዜ ወደ ደሴ ሆስፒታል ሄጄ በመረመር ዶክተሩ መርምሮ ለ፲፱፻፹፩ ዓ/ም ለየካቲት ፲፩ ቀጠሮ ሰጠኝ ለምንድን ይሆን ብዬ በጠይቅ ኦፕራሲዮን ልትሆኚ ነው አለኝ እኔም በቃ አንድ ቁርጤን አውቃለሁ ብዬ ስቀመጥ ጥር ፲፫ ለ፲፬ አጥቢያ ሌሊት ተኝቼ ህልም አየሁ ህልሙም ቀጠሮዬ ደርሶ ወደ ሆስፒታል የሄድኩኝ ይመስለኛል እዛ ሆስፒታል ስደርስ ዶክተሩ ወደ ኦፕራሲዮን ክፍል ያስገባኝና አስተኝቶኝ እንዳስ መርፌ ሊወጋኝ ሲል መብራቱ ይጠፋል ሲጠፋም ዶክተሩ በጣም ይናደዳል ከዛ መብራቱ ይበራል ወዲያውኑ በጣም ቀይ የሆነ ትልቅ ሰው አባቴን ይመስለኝና ከበሩ ላይ ቆም ብሎ ያንኳኳል ምንድን ነው አባባ ምን ይፈልጋሉ ብሎ ዶክተሩ ይጠይቀዋል አባቴም ልጄን ኦፕራሲዮን እንዳታደርጋት እኔ አልፈቅድም ሲለው ጊዜ ሐኪሙም በጣም ተናዶ ለምን ሲል ጠየቀው እሷ ምንም አታውቅም ልቀቅልኝ ሲለው ከአልጋው ላይ አስወርዶ በቁጣ መንፈስ ከበሩ ሲያስወጣኝ አባቴም ቀኝ እጆቼን ይዞኝ ለምንድነው ሐኪም ቤት የመጣሽው የእንቺ አባት እኮ አቡነ አረጋዊ ናቸው እሳቸው ናቸው የሚያድኑሽ እያለኝ ከሆስፒታሉ በር ስንወጣ ባነንኩኝ ።

ከዛ ቀን ጀምሮ ሆስፒታል ብሔድ የምሞት መስሎ ይታየኝ ጀመር በኋላም መሄድን ትቼ የአቡነ አረጋዊን እምነት ለም፯ ሰውነቴን መቀባት ጀመርኩኝና እየተሻለኝ ሄደ ግን እንደዚያም ሆኖ ለ፫ ዓመት ያክል የጨጓራ ኪኒን እየወሰድኩኝ ማለትም ፲፱፻፹፯ ሐምሌ ወር ድረስ እውጥ ነበር ። ከዛ በመጨረሻ ጊዜ የትንፋሽ ማጠርና የቀመስኩት ነገር እምቢ ውስጥ አልረጋ አለኝ ሌሊትም ቀንም ሥቃይ ሆነ ለእኔ ሁለቱም ወቅቶች አንድ ሆኑብኝ ተሰቃየሁ ቤተሰቡ በሙሉ ግራ ገባቸው ከተኛሁበት መውረድ ይቅርና ከጎን ጎኔ መገላበጥ ተሳነኝና ተረታሁኝ እንደዚሁ እየተሰቃየሁ ሁለት ወር በመኖሪያ ቤቴ ታመምኩኝ በዛን ሰዓት የምግብ መርፌ ብቻ ነበር የምወስደው ሌላ ምንም ዓይነት ነገር አልወስድም ነበር በኋላ መስከረም ፫ ቀን እራሴን ስስት ያለሁበት ሲጠፋኝ ወደ ላይ ማለቴ አላቋርጥም ሲል ወደ ደሴ ሆስፒታል በስትሬቸር ተጉዠ ሄድኩኝ እዛም ልክ ከቀኑ በ፰ ፡ ፴ ነበር የደረስነው ዶክተሩ መርምሮኝ ባለቤቴን ጠርቶት ለምን እንደዚህ እስከምትሆን አቆያችኋት ብሎ ተቆጥቶ አሁን ይህቺ ልጅ ምንም ዓይነት ምግብ እንዳትበላ ውሀም እንዳትጠጣ የሚታዘዝላት አንድ እጅ ወተት ሁለት እጅ ውሃ እየተፈላ በቀን ፫ ስኒ ብቻ ነው ምክንያቱም ጨጓራዋ ከፍተኛ ጉዳት ላይ ደርሷል ። እዚሁ ሆስፒታል ትተኛ ብሎ አስተኛኝና የምግብ መርፌ ተቀከለልኝ መድኃኒትም ታዘዘልኝ እሱም መድኃኒት በሆስፒታሉ ውስጥ የለም ነበር ከግል ፋርማሲ ፱ መርፌ በ፺ ብር ተገዛና መጣ ቤተሰቦቼም ሆስፒታሉ ምንም እንደማይረዳኝ አወቁ መስከረም ፮ ቀን ወንድሜ ከዶክተሩ ተነጋግሮ ሁለተኛ አላሳክምም ብሎ ፈርሞ ያለዶክተሩ ፈቃድ ወደ ቤት ይዘውኝ ተመለሱ እቤትም ከገባሁ በኋላ የምግብ መርፌው አላቋረጠም በዛው ላይ የመድኃኒት እይነት ይሰጠኝ ነበር እኔም እስከ መስከረም ፲፪ ቀን ድረስ ያለሁበትን ቦታ ምንም አላውቅም ነበርና መስከረም ፲፭ ማታ በ፫ ፡ ሰዓት እንደ ህልም ነገር ታየኝ ህልሙም ከገደል ሥር የተሰራ ትንሽ ጠባብ ቤት ውስጥ ልገባ ስል ጠይም ሰውዬ ተመለሽና ወደ ላይ ወጥተሽ ደስ ከሚልሽ ጸበል ቅጂ እና ታጠቢ ከዛ በኋላ ወደ ቤትሽ ሂጂ ሲለኝ ሂጄ ከጸበሉ አጠገብ ቁጭ ስል ብንን አልኩኝ አሁን ግራና ቀኝ ዙሪያው ሕዝብ ግጥም ብሎ እናቴ በቀኝ እጅዋ ደረቴን ያዝ አድርጋኝ ወንድሜ የምግብ መርፌ የተሰጠሁበትን እጄን ይዞ ያለቅሱ ነበር ምነው ብላ እናቴ እየት አደረገች እና ጠራችኝ ምንም አልሆንኩኝም እንደዚህ ዓይነት ህልም አየሁ ብዬ ነገርኳት እና እሷም ጠበሉ የማን ጠበል መሆኑን አውቀሽዋል አለችኝ እኔም አላወኩትም ብዬ መለስኩላትና ከዛን ቀን ጀምሮ ነፍሴን አወኩትና ከዛ በኋላ በወተትና በምግብ መርፌ ብቻ ስሰቃይ ቆይቼ በኅዳር ፩ ቀን እስኪ ጤና ጣቢያ ትሂድ እዛ ጥሩ ሐኪም አለ ተብሎ ደሴ ጤና ጣቢያ ወስዳኝ ዶክተሩም መርምሮ ለምን እስከአሁን አልታከምሽም ብሎ ጠየቀኝ እኔም ታክሜ ነበር ግን አልተሻለኝም ስለው ሀኪሙም ቢያንስ በቀላሉ ለ፪ ወር በሆስፒታል ተኝተሽ ተከታተይ ህክምና ነው የሚያስፈልገሽ አለኝ እኔም ደሴ ሆስፒታል ተኝቼ ነበር ግን አንድ ቀን አድራ ነው የወጣሁት ስለው ማን ነው ያስወጣሽ እንዴት አይነት ሀኪም ነው ብሎ ተቆጣ እኔም አይ ማንም ሁጪ ያለኝ የለም ገንዘብ ስለሌለኝ ብቻ ነው ታዲያ ገንዘብ ከሌለሽ አሁን እዚህ ለምን መጣሽ በሽታሽ እንኳን በጣም ከባድ ነው የጨጓራ በሽታ ሲባል ቀላል አይደለም ጨጓራሽ ከመጠን በላይ ቆስሏል ስለዚህ ነው በአፍሽ ደምና መግል የሚወጣው ምራቅ የማያቋርጠው ለዚህ ነው እንጂ እንደ ቀላል አትይው እራስሽን ለማስታመም ዋከሪ ግን አሁን ገንዘብ ከሌለሽ እንዴት ለአንች የሚሆን መድሃኒት ማዘዝ ይቻላል ብዙ ብር ይፈልጋል እና ለጊዜው የሚረዳሽ ኪኒን እና ሽሮፕ ግዢና ውሰጅ መድሃኒቱን ስትጨርሺ ነይ ብሎ የ፩ ወር መድሃኒት ሰጠኝና ወደ ቤቴ ሄድኩኝ ከዛ መድኃኒቱን ስውጥ በአፌ የሚወጣው ቆሻሻ እና ምራቅም መቆም ጀመረ ከዛ እንደዚያ እያልኩ ለ፲ ቀን ያክል ከዋጥኩኝ በኋላ ኅዳር ፲፩ ቀን ከቀኑ በ፯ ሰዓት ጀምሮ በጣም የተጣደፈ ትውከትና ማንቀጥቀጥ ጀመረኝ ከቴቀመጥኩበት ዝርግትግት ብዬ ስወድቅ እረፍት የሌለው ትውከት እየቀጠለ ሲሄድ ባለቤቴም እየጎኛና ተደናግጦ ጎረቤት ጠራ ወደ እናቴም ተላከባት እየሮጠች መጣች እኔም ምን እንዳስመለከተኝ እንጃ የአቡነ አረጋዊን እምነት ቅቡኝ ብዬ ወደኩኝ ከዛ እንስተው አልጋ ላይ ዘረጉኝና ትንፋሽ አጠረኝ ከሁለት ጡቴ መሐል የሆነ ነገር ዘጋኝና አይኔ ብቻ ፍጥጥ አለ ቢጠሩኝ መልስ መስጠት አልቻልኩም በዚህ ጊዜ ወደ ወላጅ አባቴ ወደ አ/አ ስልክ በ፱ ሰዓት ተደወለ እና ለቀብር እንዲደርስ ተጠራ አባቴም ሰምቶ ደንግጦ መጣ እኔም እስኪ ፲፪ ሰዓት ድረስ ምንም አላውቅም ነበር በመጨረሻ አንዲት ሴት እምነቱን በጥብጣ አፌን በእጅዋ መልጋጋ ስትግተኝ የአነቀኝ ነገር እየተንከባለለ ወደ ባሕር ሆዴ ሲገባ እህ ተነፈስኩ ብዬ ስናገር ቅዠት ነው ይሉ ነበር እረ አይደለም ያነቀኝ ነገር ወደ ሆዴ ገብቷል አንሱኝ ስላቸው ሁሉም ተገረሙና ጨጓራዋ አንቋት ነው እንጂ ተመለሰላት ብለው ቁጭ አደረጉኝ ። እየተሻለኝ መሄድ ጀመረ ሌሊቱንም በሰላም ተኝቼ አደርኩኝና ሲነጋ ጭራሽ የታዘዘልኝን መድኃኒት መዋጥ አስጠላኝ ሳልውጥ ተውኩት አባቴም ልክ ኅዳር ፲፭ ቀን ከምሽቱ በ፲፪ ሰዓት መጣ እሱም በሕይወቴ ሲያገኘኝ ከፍተኛ ደስታ ተሰማውና ልክ ኅዳር ፳ ቀን ከደሴ ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ጀመርን አ አ ከመጣን በኋላ ወደ ሆስፒታል ከመሄዳችን በፊት ጸበሉን ልጀምርልሽ ብሎ አባቴ ጠየቀኝ እኔም እሽ ብዬ አባቴም አቡነ አረጋዊ እየተመላለሰ በጀሪካን እያመጣ ለ፩ ሳምንት ስጠመቅና ስጠጣ ከሆዴ ውስጥ የመንከባለል ስሜት ተሰማኝ ሁለተኛ ሳምንት ስጀምር በሽታው ከእምብርቴ በታች መሆን ጀመረና መንከባለሉን ትቶ ዝም ብሎ ግን ሰውነቴን ደስ አይለኝም ነበር ልክ ፫ ሳምንት ስጀምር ማለትም በ፲፯ ቀኔ ታኅሣስ ፲፭ ቀን ከምሽቱ በሦሥት ሰዓት ቁጭ ካልኩበት የሆነ ደም ከማህጸኔ ፈሰሰ እንዴ ምንድነው ብዬ ተገረምኩኝና ታጥቤ ተኛሁኝ ተኝቼ ሳለ ሌሊቱ ፲ ሆነብኝ ጭንቅና መከራ መጣብኝ ስቀመጥ ስተኛ ከእወገቤ ድረስ በደም ጎርፍ ተነከርኩ ከዛ ሰዓት ላይ ፲ ሰዓት ሆኖአል እወገቤ ስር ትራስ አድርጌ ገደፋ እንዳልኩ እንቅልፍ ወሰደኝ ወዲያውኑ ህልም አሳየኝ ህልሙም ቀይ ሴት ነጭ የሐበሻ ቀሚስ የለበሰች እናቴን ትመስለኝና ትመጣና እዚህ ቤቶች ብላ ስትጣጣ እኔ ምጥ ይዞይ አለቅስ ነበር ውይ ልጄ ምነው ብቻሽን ታለቅሻለሽ ትለኝና ትመስኖለች እኔም ምጥ ይዞኝ የሚገድፈኝ ሰው አጥቼ ነው ስላት አይዞሽ እኔ ደርሻለሁ በይ ነይ ብላ እቅፍ አድርጋ አመራት እጠራዳ ሁለት እግሯ መሀል አድርጋ ወገቤን እቅፍ ታደርገኝና በይ አይዞሽ ግን መቼ ያረገዝሽውን ልጅ ነው የምትወልጅ ብትለኝ እያስማጠኝ ነው እኮ ስላት ሆድሽ የታለ ብላ ስትዳስሰኝ ወዲያውኑ ወለድኩኝ ስወልድ ሽፍን ብሎ የማይታወቅ ነገር ነበር እስኪ ልየው ግለጭው ስላት ይሄ እንኳ እንቺ አታይውም ህዝብ ነው የሚያየው እንኳን የተገላገልሽልኝ ብላ እቅፍ እንዳደረገችኝ ብንን ስል ያሰጨንቀኝ የነበረው ምጥ ለመውጣት ወደ ቻች ገዝቆ ብሎ ቆዳዬን ልጥጥ አድርጎ ይዞኝ ነበር በዛን ሰዓት ልክ ፲፪ ሰዓት ነበር ትንሽ ቆይቼ ወደ ሽንት ቤት ቀስ እያልኩ ሄጄ ቁጭ ስል ከብዙ ደም መፍሰስ በኋላ ያልታወቀ አውሬ ሲወጣልኝ ከጭንቅላቴ ጸጉር የተነቀለ መስሎ ተሰማኝና ደነገጥኩኝ ሳጥኑ ጠርቼ ውሃ ላይ ተቀመጠና የመጣው ሰው ሁሉ እያየው ይመራመርበት ጀመር ግማሹ ሰው ሆስፒታል ሄዳ ልጅቷ ትመርመር ይህ አውሬ የጨፋ በሽታ ብሰውነቷ ላይ ጥሎባት ይሆናል እያሉ ሲናገሩ እኔ ግን እሱ የፈጠረኝ ጌታ እሱ የጀመረውን እሱ ጨርሶ ይምረኛል እንጂ ሀኪም ቤት አልሄድም ብዬ ቀረሁኝ ከዛ አውሬው ከወጣበት ቀን ማለትም ከታኅሣሥ ፲፪ ቀን ጀምሮ እስከ ታኅሣሥ ፳፭ ድረስ ከፍተኛ ደም ይፈስኝ ነበር ሲፈሰኝም ዝም ብዬ ጸበሉን ስጠጣ እና ስጠመቅ በ፳ ቀኑ አቆመልኝ እኔም ለጌታዬ ክብር ምስጋና ይድረሰው ብዬ ታኅሣሥ ፳፩ ቀን ተአምሩን ለመናገር ወደ አቡነ አረጋዊ ቤተ ክርስቲያን ሄድኩኝ እኔ ግን ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስን ተመስገን ብዬ በምርኩዝ ደርሼኩኝ በ፲፱ ዓመቱ ቤተ ክርስቲያን ደጅ ስረግጥ መስቀል ስሳለም የተሰማኝ ደስታ ይሄ ነው ብዬ ለመናገር ቃላት ያጥሩኛል ። እንዲያው በደፈናው ተመስገን ብቻ ነው ።

ስለዚህ አምላክ አቡነ አረጋዊ አምላክ ቅዱሳን ክብር ምስጋና ይድረሰው በአባቴ በአቡነ አረጋዊ ተራዳኢነት በአመቤቴ በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ከባለዛርነት አውጥቶ ለፈጠረኝ ጌታ እንድሰግድለት ላደረገኝ ጌታዬ መድኃኒቴ ኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጋና እያቀረብኩ በሚቀጥለውም ሕይወቴ በፍጹም ልቤ በፈቃዱ እንድመላለስ እየጸለይኩ እኖራለሁ ። በማለት በጸድቱ

www.ethiopianorthodox.org

ቅራጻኢነት የተፈጸመላቸውን እጹብ ድንቅ የሆነ ገቢረ ታምራት ገልጸዋል ።

መሪጌታ ኤፍሬም በየነ

# የማይናገሩት ባሕታዊ

ለ፶፭ ዓመታት ከሩ ከመናገር እንደበታቸውን የዘጉ ከመናገር ብለው በዝምታ በአንድ የተወሰነ ቦታ ውስጥተወስነው የኖሩት አባ እርምሞ ለተቀመጡበት ቦታና በአካባቢው ለሚኖሩ ሕዝቦች መድሃኒት ሆነው መገኘታቸው በይፋ ይነገርላቸዋል እኛም በአጋጣሚ ልናነጋግራቸው ባንችልም መልካቸውንና መንፈሳዊ አቋማቸውን ለማየት ታድለናል እኒሁ አባ በጸጉራቸው መሸፈንና ከቆዳ ልብሳቸው ጋር ሲታዩ በመንፈሳዊ ውበታቸው እጅግ በጣም ያማሩና የተወደዱ ሆነው ታይተዋል ።

ለ፶፭ ዓመታት እንደበታቸውን ዘግተውና ከመናገር ተቆጥበው አሁን ባሉበት ቦታ በትዕግሥት ተወስነው የኖሩት አባ አእርምሞ በአሁኑ ሰዓት ከ፹፯-፺፭ የሚጠጋ ዕድሜ አላቸው ተብሎ የሚነገርላቸው ሲሆን በገጽ ሲታዩ ግን ከ፷ ዓመት በላይ ይኖራቸዋል ተብሎ አይታሰብም አካሄዳቸውና አቋማቸው ሲመዘን የእርጅና ባህርይ አይታይባቸውም ።

አባ እርምሞ በዚሁ ደምጣ ደብረገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ተወልደው ያደጉ ሲሆኑ በቃል በመናገር በመጻፍና በማንበብ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈሳዊ አገልግሎት በመስጠት የኖሩ አባት ነበሩ ከዕለታት አንድ ቀን ከሕዝብ መካከል አንድ ግለሰብ አስቀይተ'ኣቸው ከዛሬ ጀምሮ ከእግዚአብሐር ጋር እንጂ ከሰው ጋር አልነጋገርም ብለው በሐዘን ለብዙ ዓመታት ከሰው ተለይተው ከኖሩ በኋላ በአፋቸው ላለመናገር ወስነው በዚሁ ውሳኔአቸው መሠረት ከ፶ ዓመታት በላይ በውሳኔአቸው ጸንተው ይገኛሉ ይህ ንንም ሲያደርጉ በቂ የሆነ ምክንያት እንዳላቸው እናያለን ።

አባ እርምሞ በዚሁ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚገኙ ልዩ ልዩ የዛፍ ዓይነቶች (አጸዶች ) ውስጥ በታሪካዊነት በተመዘገበው ወይራ ስር ባለው ጥልቅ ዋሻ ውስጥ ጸሎታቸውን ያካሒዳሉ የጸሎታቸውም ሰዓት ከጠዋቱ ፲፪ ሰዓት እስከ ምሽቱ ፩ ሰዓት ሲሆን ከአንድ ሰዓት በኋላ ይወጣሉ በዚህም ሰዓት ከዋሻ ውስጥ የሚወጡት በጣም ፈዋሽ ወደሆነው የደምጣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ጠበል የሚመጡትን ሕሙማን (ጠበልተኞች ) እግራቸውን አጥበው የሚያርፉበትን አዘጋጅተው ለማስተናገድ እንዲችሉ ነው ። ሕሙማኑም በእሳቸው እጅ መዳሰስ ስለሚፈልጉ ከበታቸው ሲኑሱ የአባ እርምሞን በረከት እግዚአብሐር እንዲያሳጣቸው እየለመኑት ይጓዛሉ በመሠረቱም አባ እርምሞ በዚህ ጉዳይ ተሰርፈው ይገኛሉ ።

አባ እርምሞ በዚህ አሠራራቸው መመሪያ አድርገው የተከተሉት «እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ እናንተ ደግሞ እርስ በእርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ



ዝምተኛው ባሕታዊ አባ እርምሞ እኒህ ናቸው

ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁ እና »'የሚለውን ነው ፤ ዮሐ ፲፫ ቁ ፲፬ ።

አባ እርምሞ በሌላ በኩል መመሪያ አድርገው የተከተሉት «እንግዳ ሆኜ ብመጣ ተቀብላችሁ አስተናግዳችሁኛልና ፣ - - - እናንተ የአባቴ ብሩካን ወደኔ ኑ የሚለውን አምላካዊ ቃል ነበር ማቴ ፳፭ቁ ፴፩ ።

እንግዲህ የአባ እርምሞን መንፈሳዊ ታሪክ በዝርዝር ለማቅረብ ያስቸግራል ሆኖም ግን በአፋቸው አይናገሩ እንጂ አሠራራቸውን የሚያውቅ የደብሩ ካህን ባለበት በበእታቸው ላይ ለተገኘ ሰው ለችግሩ መፍትሔ አግኝቶ መመለስ ይችላል በመነሻችን ላይ ለቦታውና ለነዋሪው ሕዝብ መድሃኒት ሆነው ይኖራሉ ያልነው ከእግዚአብሐር በተሰጣቸው ጸጋ ለችግረኛው ሁሉ መፍትሔ ለመስጠት በመቻላቸው ነው ።

አባ እርምሞ ስለአንደበታቸው መዘጋት ምክንያት የሆነው የምስክርነቱ ጉዳይ ነው ተብሏል ከእግዚአብሐር ቃል እንደምንማረው ደግሞ «ከአፍ የሚወጣ ከልብ ይወጣል ይህም ሰውን ያረክሰዋል «ይላል (ማቴ ፲፭ ቁ ፲፰) በሌላ በኩል የእግዚአብሔር ቃል ሲያስተምረን » አሁን ግን እናንተ ቁጣንና ንዴትን ክፋትንም ከአፋችሁ ስድብንም የሚያሳፍርንም ንግግር እነዚህንም ሁሉ አስወግዱ ይለናል ፤ (ቆላ ፫ቁ ፰)

አባ እርምሞ መጻሕፍ|ን ሲያነቡ መጻሕፍት መካር ወንድሞች ናቸው ይሉ ነበር አፋቸውን ከመዘጋታቸው አስቀድሞ በዚህም ወቅት የምናቀርበው ጥቅስ «አንደበት እሳት ነው አንደበት በብልቶቻችን መካከል አመጸኛ ዓለም ሆኗል ሥጋን ሁሉ ያሳድፋልና - - - «ያዕ ፫ ቁ ፮ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለኤፌሶን ሰዎች ሲያስተምር» ለሚሰሙት ጸጋን ይሰጥ ዘንድ እንደሚያስፈልግ ለማነጽ የሚጠቅም በጎ ቃል እንጂ ከአፋችሁ ክፉ ቃል አይውጣ » ይል ነበር (ኤፌ ፬ ቁ ፳፱-፴፪) ይሄን የመሳሰለው አምላካዊ ቃል ለእርምሞ ማጠናከሪያ ሆኗቸዋል ።

እንግዲህ አባ እርምሞ ለመንፈሳዊ ቁም ነገር የተዘጋጀ ህይወት ስለነበራቸው ሰውን ከማማት ሰድቦ ከማስቀየም እንድድን ብለው አንደበታቸውን ዘጉ « አባቱን ወይምእናቱን የሰደበ ፈጽሞ ይሙት » (ማቴ ፲፭ ቁ - ፬) ይህ ቃል አባትና እናት ማለት በሥላሴ አምሳል የተፈጠረ ሁሉ በመሆኑ የሞት ሞት እንዳይፈረድብኝ ብለው ለ፶፭ ዓመታት ከማንም ጋር ሳይነጋገሩ በጾማቸው በስግደታቸው በጸሎታቸውና በመልካም ሥራቸው በደምጣ ጊዮርጊስ ውስጥ ልዩ መንፈሳዊ ሰው ሆነው እንዲኖሩ እግዚአብሔር እንደፈቀደላቸው እናያለን ።

አባ እርምሞ ያሉበትን ዋሻ ለቀው ሲወጡ መናንያን ጓደኞቻቸው በዋሻ ውስጥ የጸሎት ተግባራቸውን እንደሚያካሄዱ የሚታወቅ ሲሆን አባ እርምሞ ግን በአዲስ አበባ በቁስቋም ቤተ ክርስቲያን አርፈው በዝቋላ በደብረሊባኖስ ፣ በደብረ አሰቦትና በመሳሰሉት ታላላቅ ገዳማት ደርሰው ሲመለሱ በማንም ግለሰብ ቤት ውስጥ እንደማይገቡ ይታወቅላቸዋል ።

አባ እርምሞ ስለቅድስና ህይወታቸው ያገኘነው ተጨማሪ ማረጋገጫ ወደ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ዘንድ በ፲፱፻፸፱ ዓ.ም መጥተው ስላሉበት ቦታ ያላቸውን ሐሳብ በደብዳቤ አቅርበውላቸው ፣ ቅዱስነታቸው ቀጠሮ ይሰጧቸዋል ፤ አባ እርምሞ በምልክታቸው እርስዎ ያንጊዜ የሉም አሏቸውና ወጥተው ሄዱ ቅዱስነታቸው ም ሌሊቱን በጸሎታቸው ሰዓት አባ እርምሞን በመንፈስ አግኝተዋቸው በሁኔታው ሲፀፀቱ ካደሩ በኋላ ሲነጋ ቄስ አዲስን አስጠርተው እኝህን አባት ፈልገህ አስመጣልኝ ብለዋቸው አባ እርምሞ እንዲመጡ ተደረገ ፣ አባ እርምሞም መጡ ቅዱስነታቸውም በአክብሮት ተቀብለው የጠየቁት ተሰጣቸው ይህ ሁኔታ የሁለቱንም ቅድስና አረጋግጦልናል ።

ስለዚህ አገራችን እንዲሁም ቤተ ክርስቲያናችን በውስጧ የሚኖረው ህዝብ ሁሉ ፣ልዩ ልዩ መከራ ተጠብቀው የሚኖሩት በነዚህና እነሱን በመሳሰሉት ቅዱሳን ጸሎት ስለሆነ እኛም እንደነዚህ የመሳሰሉት አባ ዮች የሚኖሩባቸውን ገዳማትና አድባራት መርዳትና ማክበር ይገባናል ።

በመጨረሻ የምንገልጸው ከአባ እርምሞ በረከታቸውን የተሳተፉ ሰዎች በአሁኑ ሰዓት የደምጣ ምክህ ደናግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን አሰርተው ምሥጋናን አግኝተዋል ፣ ይህን ታሪክ ስናቀርብ እስከአሁን ላላወቃችኋቸው እንድታውቁአቸውና ፣ በረከት እንድታገኙ አስበን ነውና እግዚአብሔር ለበረከቱ ያብቃችሁ እንላለን ።

ጻድቁ አባ እርምሞ የሚገኙበት በሰሜን ወሎ ሀ/ስብከት በየጁ አውራጃ በጎባ ለፈቱ ወረዳ ውስጥ ነው ።

ቄስ ሐዲስ ነጋሽ

# የጋሥጫ አባ ጊዮርጊስ ገዳም ታሪክ

ኢትዮጵያ ሀገራችን በተፈጥሮ የታደለች ገና ያልተጠቀምንበት የማዕድን ክምችት የሚገኝባት ዘብታምና ንጹህ ተስማሚ የአየር ጸባይ ያላት ሀገር መሆኗን የተለያዩ ምሁራን መስክረውላታል ከዚህም ባሻገር የኢትዮጵያችን የታሪክ ጉዞ ከክርስትና ሕይወት ጋር የተጣመረ እንደመሆኑ መጠን ሀገራችን ኢትዮጵያን ጥንታዊት ታሪካዊት ከሚያሰኟአትና በዓለም ዙሪያ ጉልህ የታሪክ ሥፍራ ከሚያሰጧት አንዱና ግንባር ቀደሙ የጥንታዊ ቅርሶች በውስጧ የሚገኙባቸው ታላላቅ ገዳማት ናቸው ። ከነዚህ ገዳማት ውስጥ አንዱ የጋሥጫ አባ ጊዮርጊስ ገዳም ነው ። የጋሥጫ አባ ጊዮርጊስ ገዳም በወሎ ክፍለ ሃገር በቦረና አውራጃ በከላላ ወረዳ ውስጥ ይገኛል ይህ ገዳም ዙሪያው በገደል የተከበበ ሆኖ ከመሬት ወደላይ ፸ ሜትር ያህል ከፍታ ያለው ነው ። ገደሉ የሚወጣው በእንጨት መሰላል ሲሆን አፋፍ ላይ ሲደረስ በጣም ትልቅ የእንጨት መዝጊያ ይገኛል ያንን አልፎ ከላይ ሲደረስ የመናንያን መነኮሳት መኖሪያ ያለበት ሜዳማ ቦታ ይገኛል ከዚያ አልፎ በስተምሥራቅ በኩል ጻድቁ አባ ጊዮርጊስ ገደሉን ፈልፍለው እንደላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት ቅርፅ እያወጡ ቅኔ ማህሌት ቅድስት መቅደስ አድርገው ያነጹት ቤተ ክርስቲያን እጅግ በሚያስደንቅ ሁኔታ ሠርተውት ይገኛል ። በዚህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ አስደናቂ ነገር አለ ይኸውም በመቅደሱ በስተሰሜን ምሥራቅ አጣሪያው ላይ ገደሉ ተሰንጥቆ ስማዩ ወለል ብሎ ይታያል ይህም አባ ጊዮርጊስ ሰዓታት ዘሌሊት እየደረሱ ሳለ ብርሃን ፈተሽ ይገባል ... [illegible] እንደወደደ ያደርጋል እንደ እስበም ይፈጽማል ብለው ዝም ቢሉ መልአኩ ያንን በመቅደሱ አናት ላይ ያለውን ገደል በሰይፉ ሰንጥቆ ብርሃን በማስገባት አልቦ ዘይከል ተሣስዮ ወአልቦ ዘይብሎ ምንተ ገብር ከእርሱ ጋር ... ሊመሳሰል የሚችል ማንነው ምን ሠራህ የሚለውስ ማን ነው ብሎ እንጂ ለምን ዝም አልክ በማለት በደርሰታቸው ላይ ይህንን መልአኩ እንደጨመረውያነገራል ።

ይሁን እንጂ መልአኩ የሰነጠቀው ገደል እስከ ዛሬ ለመቅደሱ ብርሃን በመስጠት ላይ ሲሆን በክረምት ዝናምና ጎርፍ በላዩ ላይ ሲወርድ ወደ መቅደሱ ግን ጠብታም አይወርድም ግን ወደላይ ሰማዩ ይታያል ይህ እጅግ አስደናቂ የሆነ የእግዚአብሔር ታል ኪዳን በዚህ በአባ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይታያል ሌላው አባ ጊዮርጊስ የሠሩት አስደናቂ ተአምር በዚህ በጋሥጫ ገዳም ባሻገር የአባ ጽጌ ድንግል ገዳም ይገኛል ። አባ ጊዮርጊስና አባ ጽጌ ድንግል በአንድ ዘመን እንደነበሩ ገድላቸው ይናገራል ታዲያ እነዚሁ ሁለቱ አባቶች

www.ethiopianorthodox.org

በጣም ስለሚፋቀሩ በገዳማቸው መካከል ወለቃ የሚባል ታላቅ ወንዝ ስላለ ሁለቱም እዚያ ድረስ እየተገናኙ ስለ ተገለጸላቸው ምሥጢረ እግዚአብሔር እየተወያዩ በመጨረሻ ማታ ማታ በጸሎት ይለያዩ ነበረ ታዲያእንዲህእያደረጉ ብዙ እንደቆዩ በክረምት ወራት ወንዙ እየሞላ መገናኘት ስላል ቻሉና በጣም ስለተቸገሩ አንድ ቀን ታዲያ ሁለቱም ማዶ ለማዶ በወንዙ ዳር ቆመው ይጸልዩ ጀመር መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ወንጌሉ የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል ሃይማኖት ቢኖራችሁ ተራራውን ከዚህ ፈቀቅ በል ብትሉት ይደረግላችኋል የሚሳናችሁ ነገር የለም እንዳለው ሁሉ እግዚአብሔርም የእነዚህን ቅዱሳን ጸሎት ተቀበሎ የወዲያኛውን ገደል ወደዚህ የወዲህኛውን ወደዚያ አገናኝቶ በሥሩ ውሃው እንዲያልፍ በማድረግ ፬ ሜትር ስፋት ያለው ድልድይ አደረገላቸው በዚህ ድልድይ እየተሻገሩ በመገናኘት ለእግዚአብሐር ምስጋና በማቅረብ ተደስተው ሳለ በዚህ የቀናባቸው ሰይጣን ይህን ድልድይ እነሱ ማታ ሲሄዱለት መቆፈሪያ ይዞ ለመደርመስ ሲቆፍር አባ ጊዮርጊስ በመንፈስ ቅዱስ ተገልጾላቸው ከነበሩበት በዓታቸው ተነስተው ወደ ወንዙ በመውረድ ከወንዙ ሲደርሱ ሰይጣን ድልድዩን ሲቆፍር አገኙት እንዳይሸሽ በመስቀል አማትበው ዘልለው ጉሮሮውን አንቀው ያዙትና በወንዙ ዳር ከሚገኘው ድንጋይ ቁመቱ ፪ ሜትር የሆነ ፲ ማዕዘን ቅርፅ ያለውን ድንጋይ አሸከመው በገዛ መቆፈሪያው ከኋላው እየወጉ ይዘውት ወደ ጋሥጫ ገዳማቸው ሲወጡ በመሰላሉ ከወጣ በኋላ አፋፉላይ ሲደርስ ድንጋዩን ወደኋላ በአባ ጊዮርጊስ ላይሊጥልባቸውሲልበመስቀላቸውቢያማትቡበት በእራሱ እግር ላይ አርፎ እግሩን ሰብረው ድንጊያውም ከላዩ ላይ አንድ ክንድ ያህል ተሸርፎ እስከ አሁን ከመሰላሉ ጫፍ እመዝጊያው አጠገብ ይገኛል ቀሪው አንድ ሜትር ከሃምሳ የሚሆነው ደንጊያ እስከ ዛሬ ድረስ በታላቅ ግንድ ላይ ተሰቅሎ በገዳሙ የሚኖሩት መነኮሳት የዕለት ምግባቸውን በሚከፋፈሉበት ሰዓትና እንዲሁም ለስብሰባ ጊዜ በደወልነት እየተጠቀሙ በት ይገኛል ።

የጻድቁ አባታችን አባ ጊዮርጊስ የደረሱአቸው በገዳማቸው አሁን የሚገኙት መጽሐፈ ሰዓታት ዘሌሊትና ዘመዓልት እንዲሁም አርጋኖን ዕንዚራ ስብሐት ውዳሴ መስቀል መጽሐፈ ምሥጢር ሆህተ ብርሃን የተባሉና ሌሎችም ስማቸው ያልተገለጸ ከእዚህ ጋራ አሥራ አንድ መጻሕፍት የደረሷቸውና በእጃቸው የጻፉቸው ይገኛሉ ። ሌላው በዚህ ገዳም በአሁኑ በዘመናችን ፤ የተፈጸመው አስደናቂ ተአምር ነው በ፲፱፻፸፫ ዓ/ም በየካቲት ወር በዚህ ገዳም አንድ አሣዛኝ የሆነ ታሪክ ተከሰቶ ነበር ይኸውም የገዳሙ መነኮሳት የኪዳነ ምሕረትን በዓል ለማክበር በአካባቢው ከምትገኘው የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን ሄደው ሳለ አንድ የክርስትና እምነት የሌለው አማጺ ወ ሰሎቹን አስተባብሮ የገዳሙን በር ሰብሮ በመግባት የገዳሙን የግብር አዳራሽ መስጊድ በማድረግ እጣን በማስጨስ ድቤ በማስመታት ጭፈራውን ሲያቀልጥ ያድራል ይህ በዚህ እንዳለ በማግሥቱ ጫት አቅርቡ ብሎ ያዛል ወዲያው ጫት ይዘው መጥተው ሲሰጡት ሊበላው ሲል ብሣና ቅጠል ይሆንበታል አሁንም እንደዚያው እየሆነ ያስቸግረዋል ከዚያ በኋላ መነኮሳቱ ለአካባቢው የሙንግስት ተጠሪዎች አመልክተው ከገዳሙ እንዲለቅ ሲደረግ ወዲያውኑ አጅበውት ከነበሩት አምስቱአማጽያን ያለምንም ጠብ በአውቶማቲክ ጥይት ሲያልቁ መሪውግን ልብሱን ጥሎ በመቀወስ እስከአሁን አገር ላገር እየዞረ እንደሚገኝ የገዳሙ መነኮሳት እንደ ታላቅ ታሪክ ይናገራሉ ይህን ከዚህ በላይ ያቀረብነውን ታሪክና ተአምር ለአብነት ጠቀስነው እንጂ በገዳሙ ደርሶ ለተመለከተግንበርካታታሪክናአስደናቂ ተአምር በስፋት ማየትና መስማት ይችላል ።

ስለዚህ የጋሥጫ አባ ጊዮርጊስ ገዳም ታላቅ የቅርሥ ባለቤት ከመሆኑም ሌላ የኢትዮጵያው ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ከፈጣሪያቸው የማይታበል ህያው ቃል ኪዳን የተቀበሉበትና በአሁኑ ሰዓትም ለዓለም ሰላምን ለሕዝብ ክርስቲያን ይቅርታና ምህረትን ከእግዚአብሐር እየለመኑ የሚኖሩ በርካታ መናንያን መነኮሳት ያሉበት ሲሆን ገዳሙ ከተመሠረተ ፳፻፶ ዓመታትን ያስቆጠረ ገዳም ነው ይህንን ገዳም ለመጎብኘት ከአዲስ አበባ በስተሰሜን መርሐ ቤቴ ዓለም ከተማ ከደረሱ በኋላ ደራ ወረዳ ድረስ በመኪና ሂዶ ከደራ ከተማ በስተሰሜን በግምት ፴ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ገዳሙ ይገኛል ስለዚህ ምዕመናን ይህን ታሪካዊ ገዳም በመጎብኘት የአባ ጊዮርጊስ የቃል ኪዳን ልጆች ለመሆን ትበቁ ዘንድ በዚህ አጋጣሚ እና ሳስባችኋለን የአቡነ አባ ጊዮርጊስ በረከታቸው ይደርብን ወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን ።

የታሪኩ አቅራቢ መምህር ክፍለ ዮሐንስ መርሻ

የታላቁ ደብረ ዝቋላ ገዳም አስተዳዳሪ ።



# በዐለ ዕርገት

ከዘጠኙ ዐበይት የጌታ በዐላት አንዱ ዕርገት ነው ። ዕርገት ማለት ወደ ላይ መውጣት ፣ መሄድ ማለት ነው ። በዚህም የቃል አፈታት መሠረት በዐለ ዕርገት ’ ’ ስንል የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ሰማይ በክብር መሄድ ወይም መውጣት ለመግለጥ ነው ።

በዐለ ዕርገት ከትንሣኤ በኋላ በአርባኛው ፣ ቀን በስድስተኛው ሐሙስ ይከበራል ። ከትንሣኤ በኋላ በአርባኛው ቀን መሆኑንም የሚያረጋግጥልን ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ነው ዮሐ ፩ ፣ ፫ የዕርገት በዐል እስከ ፬ኛው ምእት ዓመት ድረስ እንደ ዛሬው ሐሙስን ሳይጠብቅ በጥንተ ዕለቱ ግንቦት ፰ ቀን ብቻ ይከበር ነበር ። ከአራተኛው ምእት ዓመት ወዲህ ግን ሐሙስን ሳይለቅ የግንቦትንም ወር ሳይጠብቅ ትንሣኤ በዋለ በአርባኛው ቀን ብቻ እንዲከበር በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ተወስኖአል ።

ቤተ ክርስቲያን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሰው ልጆች ድኅነት የፈጸማቸውን ድርጊቶች ሁሉ ሁል ጊዜ በታላቅ ክብር ታስታውሳለች ። ከእነዚህም መካከል ፡ ክርስቶስ የማዳን ሥራውን የፈጸመበት ዕርገቱ ስለሆነ በዓመት አንድ ጊዜ በከፍተኛ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ታከብረዋለች ። ከዚህም የተነሣ ’ ’ በዓመት ፡ እንደ ዕርገት ’ ’ ይባላል ።

መድኀን ክርስቶስ ለዓለም ድኅነት ስለፈጸማቸው ነገሮች ሁሉ ትንቢት ተናግሮአል ። እንደዚሁም ዕርገቱን በተመለከተ ነቢዩ ዳዊት አስቀድሞ ትንቢት ተናግሮ ነበር ፤ ትንቢቱም የሚከተለው ነው ።

’ ’ እግዚአብሔር በእልልታ ፡
ጌታችንም በመለከት ድምፅ ዐረገ ።
ዘምሩ ፣ ለአምላካችን ዘምሩ ፡
ዘምሩ ፣ ለንጉሣችን ዘምሩ ። /መዝ ፵፯ ፡ ፭-፮ /
ምርኮን ማርከህ ወደ ላይ ዐረግህ ፡
ስጦታንም ለሰው ልጅ ሰጠህ ።
/ መዝ ፡ ፷፯ ፡ ፲፰ / ።
በምሥራቅ በኩል ወደ ሰማይ ለዐረገ
ለእግዚአብሔር ዘምሩ መዝ ፷፯ ፴፫
ጌታ ፡ ጌታየን በቀኜ ተቀመጥ አለው።
/መዝ ፩፻፱ ፡ ፩

እነዚህ ትንቢቶች ጌታችን የማዳን ሥራውን ፈጽሞ ነፍሳትን ከሲኦል አውጥቶ ወደ ገነት አግብቶ ካረገ በኋላ በአብ ቀኝ / ዕሪና / መቀመጡንና መንፈስ ቅዱስን መላኩን በግልጥ የሚያስረዱ ናቸው ። ስለሆነም በዕለተ ዕርገቱ ይነበባሉ ፡ ይተረጉማሉ፣ ይዘምራሉም ።

ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ጌታ ያረገበትን ጊዜ ከትንሣኤው -ብኋላ በአርባኛው ቀን ብሎ እንደ ተናገረ ያረገበትንም ቦታ በግልጥ ያሳያል ። በወንጌሉ ምዕራፍ ፳፬ ቁጥር ፶ ላይ የዕርገቱ ቦታ ቢታንያ እንደሆነ ሲናገር በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ፩ ቁጥር ፲፪ ደግሞ ደብረ ዘይት መሆኑን ተናግሮአል ። ይህም የተለያየና የማይስማማ አሳብን አያመለክትም ። ቢታንያ በደብረ ዘይት አጠገብ የሚገኝ መንደር ነው ። ደብረ ዘይት ግን የአካባቢው አጠቃላይ ስም ነው ። ስለዚህም በወንጌሉና በግብረ ሐዋርያት እነጋገር ልዩነት እለመኖሩን እንረዳለን ።

ጌታችን በደብረ ዘይት ላይ ብዙ ሥራ ሠርቶአል ። ቀን በቤተ መቅደስ ሲያስተምር ውሎ ፡ ማታ በደብረ ዘይት ያድር ነበር / ሉቃ ፳፩ ፡ ፲፯/። ነገረ ምጽአቱንና የኢየሩሳሌምንጥፋት የተናገረ ፡ በደብረ ዘይት ነው / ሉቃ ፳፩ ፡ ፳ / አቡነ ዘበሰማያትንም ያስተማረ በዚሁ በደብረ ዘይት ነው ። ስለሆነም በዚሁ ቦታ ላይ በተሠራ ገዳም ውስጥ ’ ’ አባታችን ሆይ ’ ’የተባለው ጸሎት በ፴፭ ቋንቋዎች ተጽፎ በግድግዳ ላይ ተሰቅሎ በጎብኝዎች ፡ ሁሉ ይነበባል ። በመጨረሻም ወደ ሰማይ ያረገው ከደብረ ዘይት ነው / የሐዋ ፩ ፡ ፲፪ / ።

መድኃኒታችን ከደብረ ዘይት ወደ ሰማይ ፤ በሚያርግበት ጊዜ መጨረሻ የመሰነባበቻና የመለያያ ጊዜ መሆኑን የተረዱ ሐዋርያት እጅግ አዘኑ፤ ከኀዘናቸውም የተነሣ ወደ ሰማይ እንጋጠው ሲመለከቱ መላእክት ደስ የሚያሰኝ አጽናኝ ቃል ነገሩአቸው ፡ - - - ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል ’ ’ አሉአቸው / የሐዋ ፩ ፣ ፲፩ / ። በዚህም መሠረት ጌታችን ዳግመኛ መጥቶ ፍርድ የሚፈረድበትና ዓለምን የሚያሳልፍበት ቦታ ደብረዘይት እንደሆነ ይናገራል ።

ጌታ ባረገ ጊዜ በቆመበት ቦታ ላይ ዛሬ ግንብ ተሠርቶአል ። የግንቡ ጣራ ክፍት ነው አንድ ሰው ከውስጥ ሆኖ ወደ ላይ ሲመለከት ሰማይን ለማየት ይችላል ። ይህም የሆነበት ምክንያት ሐዋርያት ፡ በዕርገቱ ዕለት ከዚሁ ቦታ ላይ ቆመው ወደ ላይ በማንጋጠጥ ጌታን እንዳዩት የዛሬዎቹም ክርስቲያኖች የዕርገቱን በዐል ሲያከብሩ ፡ እንደ ሐዋርያት በጣራው ክፍተት ወደ ሰማይ እያዩ እንዲያከብሩ ተብሎ ነበር ።

ከብሉይ ኪዳን እንደምንረዳው ሞትን ሳይቀምሱ ከእነሥጋቸው ወደ ሰማይ ያረጉ አሉ ።ከእነርሱም አንዱ ነቢዩ ኤልያስ ነው ። ይሁን እንጂ የነቢዩ ኤልያስ ዕርገት በእግዚአብሔር ትእዛዝ በእሳት ፈረሶች ። በሚሳቡ የእሳት ሠረገላዎችና በአውሎ ነፋስ እየታገዘ ነበር ፪ኛ ነገ ፪ ፤ ፩ - ፲፪ ይህም ሰዎች ምንም ቅዱሳን ቢሆኑ የሌላ ኃይል፣ ርዳታና ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ያመለክታል። የነቢዩ ኤልያስ ዕርገት ጻድቃን ለዘለዓለም ወደሚ



www.ethiopianorthodox.org

ኖሩበት ሰማይ /መንግሥተ ሰማይ / ሳይሆን ለጊዜው እስከ ዕለተ ምጽአት ወደሚኖሩበት ወደ ገነት ነበር ። በመሆኑም ኤልያስ እንደገና ተመልሶ ወደ ዚህ ዓለም እንደሚመጣና ጽዋዐ - ሞትንም እንደሚቀበል ተጽፎአል / ራእ ፲፩ ፡ ፫ - ፰/ ።

የጌታችን የኢየሱስ ዕርገት ግን በዐውሎ ፣ ነፋስና በእሳት ፈረሶች በሚሳብ ሰረገላ ወይም ፣ በመላእክት ኃይል በመታገዝ አይደለም ። እርሱ በሁሉ ላይ ሥልጣን ያለውና ምንም የሚሳነው ፣ ነገር የሌለ አምላክ ስለሆነ በራሱ ኃይል ወደ ሰማይ ዐርጎአል ። ’ ’ ደመና ተቀበለችው - - - -ከዐይናቸውም ተሰወረ ’ ’ ሲባልም ይህ ደመና የባሕርይ ከዚህም ጋር የጌታ ዕርገት እንደ ኤልያስ በገነት ለመኖር አይደለም በአብና በመንፈስ ቅዱስ ዘንድ በአለ የባሕርይ ክብሩ ለዘለዓለም ለመኖር ፣ ነው እንጂ ።

የክርስቶስ ትንሣኤ የሥጋችን ትንሣኤ የተረጋገጠበት እንደሆነ ዕርገቱም ከሙታን ትንሣኤ በኋላ ወደ ተዘጋጀላችው መንግሥተ ሰማያት የንጹሓን ጻድቃን ዕርገትን ስለሚያረጋግጥ ፤ በተዋሕዶ ቃል የባሕርይ አምላክ የሆነው ሥጋ በየማነ አብ በዘባነ ኪሩብ የተቀመጠበት ስለሆነ ቤተ ክርስቲያን በዐለ ዕርገቱን ዐቢይ በዐል አድርጋ ታከብረዋለች ። በየዕለቱም ’ ’ ነአምን ዕርገተከ ዕርገትህን እናምናለን



ዐርገ እግዚአብሔር በይባቤ ወእግዚእነ በቃለ ቀርን (እግዚአብሔር በእልልታ ጌታችንም በመለከት ድምፅ ዐረገ)

ክብሩ ነው እንጂ እንደ ኤልያስ ዕርገት የሚያግዝ ወይም የሚደግፍ መሣሪያ አለመሆኑ በቅዱሳን ሊቃውንት ተተርጉሞአል /ትርጓሜ ወንጌል ዘማቴዎስ ፲፯ ፡ ፩ /

ጌታ ከዕርገቱ በኋላ ዳግመኛ የሚመጣው ፣ በሕያዋንና በሙታን ላይ ለመፍረድ እንጂ እንደ ኤልያስ ለማስተማርና እንደገና ለመሞት አይደለም

’ ’ ዳግመ እምገ ፣
ኢይረክቦ ሞት ከመገ ።
ዳግመኛ ከዚህ በኋላ
እንደዚህ ያለ ሞት አያገኘውም ” (ያሬድ)

’እያለች ስታስበው ትኖራለች ።

በአንዳንድ አገሮች ስለ ዕርገት በዐል የተለያየ አከባበር ይታያል ። ለምሳሌ ፣ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ጌታ ባረገበት በደብረ ዘይት ላይ ያከብሩታል ። እንደ ጠረጴዛ ሆነው የተሠሩ አምስት የድንጋይ መደቦች ከዕርገቱ ቦታ ይገኛሉ ። በእነዚያ ላይ ድንኳን ተክለው ይቀድሳሉ ።

ከምዕራባውያን ክርስቲያኖች አንዳንዶች ፡፡ ደግሞ ከከተማ ወደ ገጠር ወጥተው ከፍ ባለ ቦታ ወይም በተራራ ላይ ሆነው የዕርገቱን በዐል ያከብራሉ ። ይህ ሁሉ የሚያሳየው ጌታ ያረገበትን ሁኔታ ለማስታወስ ነው ።

በሀገራችንም በአንዳንድ አካባቢ ስለ ዕርገት በዐል የተለየ ባህል አለ ። ለምሳሌ በጌታ ፣ በእመቤታችን ፣ በመላዕክት ፣ በጻድቃንና በሰማዕታት ስም የተቋቋመ ማኅበር ቢኖር የማኅበሩ ሙሴ ጠበልጸዲቅ አዘጋጅቶ የማኅበሩን አባላት የሚጋብዘው በዕለተ ዕርገት ነው ። ሙሴው ርእሰ ማኅበር እንደሆነ የዕርገት በዐል የበዐላት ሁሉ ፍጻሜ ነውና።

ጌታችን በሚያርግበት ጊዜ እጆቹን ዘርግቶ ደቀ መዛሙርቱን ባርኮአቸዋል ። በዚህም ቡራኬ እስከ ሊቀ ጵጵስና ያለውን ሥልጣነ ክህነት ሰጥቶአቸዋል ። እነርሱም ደስ ብሎአቸው ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰዋል ። እነሆ በዚህ መሠረት የዕርገቱ በዐል የበረከትና የደስታ በዐል መሆኑን እናስተውል ።

’ ’መንክር ስብሐተ ዕርገቱ ፣
የዕርገቱ ክብር ድንቅ ነው! ’ ’
መጋቢ ብሉይ ሠይፈሥላሴ ዮሐንስ

# ርክበ ካህናት

ከአባቶቻችን ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን መንፈሳውያን አበው በየጊዜው እየተሰበሰቡ የመንጋውን ጠባቂ የሚመርጡበትና የመንፈሳዊ አስተዳደርናን መመሪያ የሚያጸድቁበት ስለ ቤተ ክርስቲያን ዕድገት ስለ ወንጌል መስፋፋትና ስለ ምዕመናን ብዛት ስለ ራሳቸው የኑሮ ሁኔታ መፍትሔ ለመፈለግ የሚወያዩበት ጉባኤ ሐዋርያት ርክበ ካህናት ይባላል ። ርክበ ካህናት የሚለው ግዕዛዊ ቃል የካህናት ዓመታዊ መገናኛ ማለት ነው ። እንዲሁም ርክበ ካህናት የቅዱስ ሲኖዶስ መሠረታዊ መገኛ ማለት ነው ። የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የሆኑ ካህናት በአንድ ላይ ተሰብስበው ተመካክረው ና ተወያይተው ለየወቅቱ ለችግሮች መፍትሔ ለመስጠት ሕግ አውጥተው በውሳኔ ካጸደቁ በኋላ ለቅዱስ ሲኖዶስ ለማቅረብ የሚችሉበት ስብሰባ ነው ።

ይሰበሰቡ የነበረው ከትንሣኤ በዓል በኋላ በሐያ አራተኛው ቀን ሲሆን እንደሌሎች በዓላት ተውሳክ ያለውና በዓመት አንድ ቀን ረቡዕን ላይ ለቅ የሚከበር መንፈሳዊ በዓል ሆኖ ኖሯል ። ይህም እንግዳ ነገር ሳይሆን ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ መንፈሳዊ ሥርዓት በመሆኑ ለብዙ ችግሮች መፍትሔ አስገኝቶአል ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ዓለም ኃጢአት ሞቶ ከተነሳ በኋላ እስከ ዕርገቱ ድረስ አንዳንድ ጊዜ ለብዙዎች አንዳንድ ጊዜ ለጥቂቶቹ ደቀ መዛሙርት እየተገለጠ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት መጽሐፈ ኪዳንን ትምህርተ ኅቡአትን ሲያስተምራቸው ቆይቷል ። ወንጌላዊው ሉቃስ ከሞቱ እስከ እርገቱ እንዳስተማረ ገልጧል ። (የሐ ሥራ ፩ ፣ ፩-፲)

ይህንንም ተግባር የሚያረጋግጥልን ወንጌላዊው ዮሐንስ በምዕራፍ ፳ ከቁጥር ፲፱-፲፯ የጻፈውን ስንመለከት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጥብርያዶስ ባህር አጠገብ ለሦስተኛ ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ በተገለጠበት ወቅት ምሳ ከበሉ በኋላ የሚከተለውን ትእዛዝ ሰጣቸው ። ጴጥሮስ ትወደኛለህን? ከወደድከኝስ ግልገሎቼን ፣ ጠቦቶቼን ፣ በጎቼን ጠብቅ አለው ይህም አነጋገር ኃላፊነትን አስተዳደርን ማስተማርን በጠቅላላው የቤተ ክርስቲያንን የአመራር ውሳኔ የያዘ ከመሆኑም ሌላ ይህም ድርጊት የተፈጸመው አብዛኞዎች ደቀ መዛሙርት በተገኙበት ጉባኤ መሆኑን ሊያመለክተን ይችላል ።

ደቀ መዛሙርቱም ይህንን መነሻ በማድረግ ከትንሣኤ በኋላ በ፳፬ ኛው ቀን በየዓመቱ ረቡዕ ቀን ርክበ ካህናት ወይም የካህናት ስብሰባ እንዲደረግ ወሰኑ ።

ይህም ጉባኤ ማትያስን በይሁዳ እግር ለሐዋርያነት እንዲመረጥ አድርጓል ።
ማኅበሩንም እንዲያገለግሉ ሰባት ዲያቆናትን መርጠሾሞአል ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ካህናት ርክበ ካህናት በተባለው ጉባኤ የገዛ ችግራቸውን በራሳቸው እየፈቱ ስለ ቤተ ክርስቲያንም አመራር መፍትሔ እየሰጡ እስከ ፫፻፲፩ ዓ/ም ድረስ እየተሰበሰቡ ውሳኔ ያስተላልፉ እንደነበረ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ገጽ ፩፻፶፰-፩፻፵፬ ይገልጥልናል ። ከዚያ በኋላ ግን ስብሰባው በካህናት ብቻ መሆኑ ቀርቶ በጳጳት ደረጃ ሆነ በሀገራችን በኢትዮጵያ የካህናት ጉባኤ ወይም ርክበ ካህናት የተጀመረው በፍሬምናጦስ ጊዜ እንደሆነ ይነገራል ። በዚያን ዘመን የነበሩት ካህናት በሊቀ ካህናቱ በአንበረም ሰብሳቢነት ተሰብስበው ጳጳስ እንዲመርጡ ተደረገ ። እንበረምን ቢመርጡት ፈቃደኛ ስለአልሆነ ፍሬምናጦስ ተመርጦ ለጵጵስና ወደእስክንድርያ ተላከ ፍሬ ምናጦስም አቡነ ሰላማ በሚል ስም የጵጵስና ማዕርግን ተሹሞ ወደ አክሱም መጥቶ ሥራውን ይሠራ ጀመር ። ቀጥሎም በሥራ የሚረዳውና የሚያግዘው አንድ ሰው ስለአስፈለገው በካህናት ጉባኤ አንድ ሰው እንዲመረጥ ሐሳብ አቀረበ ። በካህናት ጉባኤ ወይም በርክበ ካህናት ሊቀ ካህናት የነበረው እንበረም ተመርጦ ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ ተሾመ ። በዚህ አኳኋን አረታዊ የነበረው ምኩራብ ሁሉ ወደ ቤተ ክርስቲያንነት ተለውጦ ወንጌል ይሰበክ ጀመር ። በዚህ ዓይነት በጊዜው ማለት በዚያ አምልኮተ ጣዖት ተስፋፍቶ በነበረበት ዘመን ብዙ መንፈሳዊ አገልግሎት እንደተከናወነ ስለ አቡነ ሰላማ የተጻፈው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል ።

በዘመናችንም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን በዓመት ሁለት ጊዜ በቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ተሳታፊነት የሚካሄደው ጉባኤ





www.ethiopianorthodox.org

ይህንኑ ፈለግ የተከተለ በመሆኑ ዛሬም በዚሁ አቢይ ስብሰባ ለቤተ ክርስቲያን የሚበጅና የሚጠቅም ውሳኔ በየጊዜው እየተላለፈ በርካታ መንፈሳዊ እን

ቅስቃሴ በተግባር እየተተረጎመ የምንመለከተው የዚሁ የቅዱሱ ርክበ ካህናት ውጤት ነው ።

ሰባኬ ወንጌል በላይ ጺጋዬ

# ድንግል ማርያም በደብረ ምጥማቅ

ደብረ ምጥማቅ ማለት በግሪክኛ ይትበሃል (አባባል) የረድኤት የበረከት የምሥጢር መግለጫ ማለት ነው ፤ ይህች ደብረ ምጥማቅ የምትባለዋ በግብጽ ሀገር ውስጥ ነው የምትገኘው የእአዋፍ ዝርያዎች በየዓይነቱ ይገኝበታል እመቤታችን ድንግል ማርያም ልጅዋን ኢየሱስ ክርስቶስን ሄሮድስ ንጉሥ ሊገለው በፈለገው ጊዜ ከዮሴፍና ከሰሎሚ ጋር ሁና ወደ ግብጽ ሀገር ተጉዛ (ተሰዳ) በደብረ ምጥማቅ በስነበተች ጊዜ ሽፍቶች እንደሚ ያስደነግጧት በኋላም ንጉሡ ሄሮድስ እንደሚሞ ትና በሰላም ወደኢየሩሳሌም እንደምትመለስ ሌላም ብዙ አስደናቂ ምሥጢሮች የተገለጸላት በደብረ ምጥማቅ ነው ።



ስእሊ ለነ ቅድሳት (ቅድስት ሆይ ለምኝልን)

በኋላም ወንጌላዊው ቅዱስ ማርቆስ በዚች ደብረ ምጥማቅ በተባለች ቦታ ለግብፅ ሕዝቦች ወን ጌልን አስተምሮ ጣኦታትን አጥፍቶ በክርስቶስ ስም ለማጥመቅና በክርስትና ሃይማኖት ለማሳመን የሚችልበትን የጥበብ ዘዴ በሕልሙ አይቶባታል ። ከዚያም የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ ዲዮስቆሮስ የተዋሕዶ ሃይማኖት የሚከበርበትን መን ገድ ለማግኘት መናፍቃን የሚመለሱበት ዘዴ ለመ

ቀየስ በደብረ ምጥማቅ ሱባዔ አድርጎ ብዙ ምሥጢር ስለተገለጸለት ይህች ቦታ ከእግዚአብሔር ጋር የም ታገናኝ መሰላል ነች ብሎ በእመቤታችን ማርያም ስም ታቦተ ሕግ ጽላት የሚኖርባት ቤተ መቅደስ አሠርቶ እንዲቀደስባት ከማድረጉም በላይ በመዓ ልትና በሌሊት የዘይት መብራት እንዲበራባት የም ህላ ጸሎት መፈጸሚያ እንድትሆን አድርጓል ።

እራሱ ሊቀ ጳጳሱም ጸሎተ ዕጣን እያደረሰ ከሳምንቱ ቀናት አንድ ቀን ማዕጠንተ ወርቁን ይዞ ያጥናት ጀመረ ከዚያም ዘመን ጀምሮ የእስክንድርያ ሊቃነ ጳጳሳት በየተሾሙበት ዘመን እስከአሁን ድረስ ጸሎተ ዕጣን አድርሰውባት ይመለሳሉ ።

ሕዝቡም በደብረ ምጥማቅ ብርሃን ሲበራባት ቀስተ ደመና ሲጋርዳት እንደኮከብ ያሉ መብራቶች ሲሯሯጡባት ስለሚመለከቱ ብዙ ሥውር ምሥጢር ይገለፅልናል እያሉ በደብረ ምጥማቅ ማርያም የሱ ባኤ ጸሎት ለማድረስ የሚጓዘው ሕዝብ እጅግ ብዙ ነው ፤ ከግብጽ ሕዝብ አልፎ በሌሎች ሀገሮች አስ ደናቂ ታሪኳ እየገነነ ሔደ ።

ከቅርቡም ከሩቅም እየተሰበሰቡ ከግንቦት ፳፩ እስከ ግንቦት ፳፭ ቀን ድረስ ከትመው ድንኳን ያላ ቸው ድንኳኖቻቸውን ተክለው የሌላቸው ድሆች ዳሳ ቸውን ልብሳቸውን ድንኳን አድርገው አምስት ቀን እየጸለዩ ይሰነብታሉ ፤ ከዚያም ዘመን ጀምሮ እስከአሁን ድረስ እመቤታችንም እየተገለጸች የየ ልቡናቸውን ሐሳብ ሁሉ ትፈጽምላቸዋለች ።

ከነዚህም መካከል በገሃድ የምትገለጽላቸው ሕልም የምትታያቸው አሉ ፤ በዚህም አስደናቂ ታሪክ እስላሞቹና አረመኔዎች ሳይቀሩ የልቦናቸ ውን ሐሳብና ፍላጎት ተገልጾ ትነግራቸዋለች ፤ ከእራሱ መዓዛን የሚጠጣውም ሕዝብ ዕጣኑን ሽቶውን ምንጣፉን ፤ መጋረጃውን ጠቅላላ ለዚች ለተቀደሰች ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ የሆነ ስጦታ እየያዘ አምጥቶ ያበረክታል ፤

ይህ በግብጽ አገር ውስጥ ሲሆን በኢትዮጵያ ደግሞ ከደብረ ብርሃን ፳ ኪሎ ሜትር በመ ኪና ተጉዞ ሰላ ድንጋይ ማርቆስ አጠገብ ደብረ ምጥማቅ ማርያም የምትባል ቤተ ክርስቲያን ትገ ኛለች ፤ ይህችም ቤተ ክርስቲያን በዓፄ ዘርዐ ያዕ ቆብ የተተከለች ናት ከዚያ ዘመን ጀምሮ በሱባኤ የጸለየባት ሁሉ የፈለገውን ሁሉ እመቤታችን ፤ በሕልሙ ተገልጻ ታናግረዋለች ፤ በግራኝ ወረራ ጊዜ ባጠገቧ በሚገኘው ዋሻ ታቦቷ ተሠውራ ኑራ በታለች የዋሻውም ስም ጻድቃኔ ይባላል የብዙ ፤ ቅዱሳን አፅም ባጠገቧ በሚገኘው ፪ኛው ዋሻ ተሠ ውሮ ምልክቱ ይታያል ።

በግብጽ የምትገኘው ተአምረኛዋ ቤተ መቅ ደስ በኢትዮጵያም መገኘቷ እመቤታችንም ለኢ ትዮጵያውያን እናት መሆኗን ያመለክታል ፤ ይህም ክዚና እንኮበር የተገኘ ነው

በእውነቱ ይህች ደብረ ምጥማቅ ማርያም ይህን ፤ የመሰለ ምሥጢር ገላጭ ስለሆነች በቦታዋ ተገኝ ተን ለዓለም ሰላም ለራሳችን የግል ችግር አንድ ሱባኤ ፪/ ሱባኤ እያልን ብንጸልይባት መልካም ነው ።

በእጅ የያዙት ወርቅ እንደ መዳብ ይቆጠራል እንደሚባለው በቀላሉ እንደዚህ ያለ ታላቅ ምሥ ጢር የሚገለጽበትን ቦታ ጥቶ ማታ ልንለያት ፤ አይገባም ቤተ ክርስቲያኒቱንም ሆነ የሱባኤ መግ ቢያዎችን ዋሻዎችን እያደስን ልንከባከባቸው ፤ ይገባል ፤ ወደጣዖት ቦታ ከመሄድ ተቆጥበን በዚች ታሪካዊ ቦታ እግዚአብሔር አምላካችንን በጸሎት እንለምነው ።

በዚህም በግንቦት ወር መጀመሪያ እመቤታ ችን የተወለደችበት ሲሆን ከግንቦት ፳፩ ቀን እስከ ግንቦት ፳፭ ቀን በግብፅ ሀገር በከፍተኛ ሥነ ሥር ዓት ይከበራል ፤ ስለዚህም እኛም ኢትዮጵያዊያን በሀገራችን የምትገኘውን ታሪካዊት ቤተ ክርስቲ ያን ሂደን እንማፀንባት እላለሁ ።

የታሪኩ አቅራቢ አባ ገ/መስቀል ተስፋየ

ዘገነተ ማርያም

---

# ጰራቅሊጦስ

ጰራቅሊጦስ ማለት መንፈስ ቅዱስ ማለት ነው ።

ይኸንንም ቃል በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ ፲፭ ፣ ፮ እንዲህ ሲል እናገኛለን«ወአንስ አማን ሀላወ እብለክሙ ይሔይሰክሙ እሑር አነ ኀበ አብ እስመ እመ ኢሐርኩ አነ ኢይመጽእጰራቅሊጦስ ኃቤክሙ ትርጓሜውም ቀዋሚ ነገር ነገርኳችሁ ወደ አብ እኔ ብሄድ ይሻለችኋል እኔ ካልሄድኩ መንፈስ ቅዱስ አይሰጣችሁምና የሚል ነው ሀብት ሆኖ ይሰጣል የሚሰጠውም ለጥቅም ነው ። እግዚአብሔር ወልድ ከእግዚአብሔር አብ እንደተገኘ እግዘአብሐር መን ፈስ ቅዱስም የተገኘው ከእግዚአብሔር አብ ነው። ሁለቱንም ያስገኛቸው እሱ ሲሆን አይቀድማቸ ውም የፀሐይ ሰሌዳው (ክበቡ ከምስራቅ ሲወጣ ብርሃኑና ሙቀቱም አብረውት ይወጣሉ ወደኋላ አይቀሩም ምሳሌውም ይኸው ነው ። በክቡቡ አብ በብርሃኑ ወልድ በሙቀቱ መንፈስ ቅዱስ ይመስ ሏልና ያዕ ፩ ፣ ፲፩ ።

እግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር ወልድ እግ ዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ተብለው ከሚመስገኑት ከሦስት አካላት አንዱ አካል ጰራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስ ነው ። ይኸውም ስም ከዘለዓለም እስከ ዘለዓ ለም ከአብና ከወልድ ጋር ለነበረው ለሚኖረው ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የሀላዌ ስሙ ነው ። ማቴ ፳፰ ፣ ፲፱ ከአብ ከወልድ ጋርበህ ላዌ በክብር በሥልጣን እኩል ነው ። በስም አጠራ ርም ያው ነው ፪ ቆሮ ፲፫ ፣ ፲፬ አብ ወልድ እግ ዚአብሔር አብ እግዚአብሐር ወልድ ተብለው እን ዲጠሩ ዮሐ ፩ ፣ ፩-፪ መንፈስ ቅዱስም እንደነሱ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ተብሎ በእግዚአብ ሔርነት ስሙ ይጠራይ ። የሐ ፣ ሥራ ፣ ፳፰ ፣ ፳፩-፳፰ ኢሳ ፣ ፮ ፣ ፫-፲ ። ፫ አካላት በአካልነታቸው ስለሚ ለያዩ መንፈስ ቅዱስም በአካሉ ልዩ ነው ዮሐ ፲፬ ፣ ፲፯

መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሰው እንኳን እራሱ የተናገረውን ሊረሳ ሌላውንም የተማረውንም ሁሉ አይረሳም ስለዚህም መድኃኒታችን እንዲህ ሲል «ወባ ሐቱ ጰራቅሊጦስ መንፈስ ጽድቅ ዘይፌኑ አብ በስምየ ውስቱ ይሜሕረክሙ ኩሎወያዜክረክሙ ነገርኩክሙ አነ » ትርጓሜውም ነገር ግን በስሜ ብታምኑ አብ የሚልክላቸው ጰራቅሊጦስ ሁሉን ይገልጽላችኋል እኔ የነገርኳችሁንም ሁሉ እንዳት ረሱ ያሳስባችኋል የሚል ነው በዚህ ቃል መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሰው ሁሉ ይገለጽለታል ሁሉንም አይረሳም በኤልሳቤጥ ላይ መንፈስ ቅዱስ ባደረ ባት ጊዜ ለማንም ያልተገለፀው ደገኛ የሆነና ከሁ ሉም የተሰወረ ይኸውም የአምላክ ሰው መሆንና የእመቤታችን ብፅዒትነት ቡርክትነት ተገልጾ ላት እናትና ልጅን ስታመሰግን አንቺ ከሴቶች ከሁሉ ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽየማኅፀንሽም ፍሬም የተባረከ ነው ብላ አመሰግናለች ይኸውም ቃል አልተረሳም በወንጌል ተጽፎአል ሉቃ ፩ ፣ ፴፱ ሌሎችም መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ቅዱሳን ሁሉ ሕያውነታቸው የቅድስት ኤልሳቤጥን ሕይወት ይመ ስላል ።

### የመንፈስ ቅዱስ ግብር

ፈሪውን ወላዋዩን እንዳይፈራ እንዳይወላ ውል ያደርጋል ስለ ሃይማኖቱ በድንጋይ ቢወግ ሩት በእሳት ቢያቃጥሉት እንዳይፈራ እንዲችል ያደርጋል ። ከብልየት ያድሳል በአእምሮ ያጉለም ሲል ያድሳልም ስንል አሁን በዘመናችን ተሐድሶ እያሉ እንደሚያወሩት ቧልትና ቀልድ ሳይሆን ከብ ሉይ ኃጢአት መለየት ክፉውን እየተው መልካ ሙን መከተል በዚያውም መጽናት ማለት ነው ምሥጢር ያስተረጉማል አንድ ቋንቋ እንኳን አከ ናውኖ መናገር የተሳነውን የዓለምን ቋንቋ አከና ውኖ እንዲናገር ያደርጋል ። መንፈስ ቅዱስ ከመ ንፈስ ሐሰት የተለየ መንፈሰ ጽድቅ /የእውነት መን ፈስ)ተብሎ ይጠራል በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ ስም የሚያታልሉ ብዙ የሐሰት መናፍስት አሉና ዮሐንስ ወንጌላዊም ይህናን በሚመለከት ሲጽፍ መንፈስን ሁሉ መርምሩ ብሎ ጽፎአል ፩ ፣ ዮሐ ፣ ፬ ፣ ፩ ፣ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሕይወት ባሕርያዊ ሕይወት ሰማያዊ ሀብት ሰማያዊ ዕውቀት



www.ethiopianorthodox.org

ክሱ የሚገኝ ሰማያዊ ኃይል ነው ጠቅለል ባለ አነ ጋገር ሀብት ስርየት ጸጋ ክብር ልጅነት ከሱ ይገኛል ምሥጢር ያስተረጉማል ቋንቋ ያናግራል ብለን ከላይ ያስቀመጥነውም ቃል ለከንቱ አይደለም እውነት ነው ።

አዳምና ሔዋንም ጸጋቸው ሳይገፈፍ ቀድሞ የእንስሳት አራዊት ቋንቋ ያውቁ ነበር ለእንስሳት ለአራዊትም ከፀብ በፊት ስም ያወጣላቸው አዳም ነበር ለምሣሌ እባብ ከጓደኝነት ፍቅርና በቋንቋ ከመግባባት የተነሳ አዳምና ሔዋንን አሳስታ ዕፀ በለስን እስከ መብላት አድርሳቸዋለች ዘፍ ፫ ፡ ፩-፯ ስለዚህም ማለት መንፈስ ቅዱስ ሰማያዊ ሀብትን ዕውቀትን የሚሰጣቸው ኃይል ስለሆነ መድኃኒታ ችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ስሙ ሕይወት መድኃኒት እንደሆነና በስሙ የኃጢአት ስርየት እንዲደረግ ከኢየሩሳሌም ጀምሮ ለሕዛብ ሁሉ ያደረገውን ታምራት ያስተማረውን ትምህርት እን ዲያስተምሩ ሂዳችሁ ሰውን ሁሉ አስተምሩ ብሎ አዞዋቸዋልና ለዚህም ሁሉኃይል እንዲሆናቸው ባረገ በአሥረኛው በተነሳ በሃምሣኛው ቀን መንፈስ ቅዱ ስን ላከላቸው እነሱም መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ዓለምን ዕፃ በዕፃ ብለው ጽንፍ እስከ ጽንፍ ዞረው ለማስተማር ገቢረ ተአምራት ለማድረግ ምሥጢረ ሰማይ ምሥጢረ ምድርን ሁሉ ለማወቅ ቋንቋ ለመናገር በየደረጃው ለዚህ ሁሉ ኃይል አገኙ ለሁሉም ደረጃ አለውና ማለት ለልሣንም ለራዕይም

ለምሳሌ ልሣንን ብንመለከት ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ የሚሰጠው እንደ አዕምሮው ስፋት እንደ ሃይማኖቱ ጽናት ነውና አንድ ሰው መንፈስ ቅዱስ ሲያድርበት አትሪኮን ቦርፎሪኮን አተር ጋዎን የሚባሉ ቃላት አሉ ። ቃለ ሰብእ ቃለ እንስሳ ቃለ መላእክት ማለት ነው ። በየደረጃው በቅደም ተከተል ይሰጡታል በመጀመሪያ በንጽሐ ሥጋ ደረጃ የአዳምን ዘር (የዓለምን ሕብረተሰብ ቋንቋና የእንስሳት የአራዊት ቋንቋ ለይቶ ማወቅ እንደ ሐዋርያት እና እንደአዳምና ሐዋን ማለት ነው ። ለምሳሌ ሐዋርያት የአፍሪካን የአውሮፓን

የአውስትራሊያን የእስያን የአረቢያን በጠቅላላ ሕብረተሰብ ቋንቋ ተናግረዋል ተርጉመዋል የሐዋ ፪ ፩-፲፱ አዳምና ሔዋንም ከላይ እንደጠቀስነው ነው ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፩-፯ ። ሁለተኛም በንጽሐ ነፍስ ደረጃ የመላእክትን ቋንቋ ማወቅ መስማት መናገር ነው እንደነቅዱስ ጳውሎስ ፪ ቆር ፡ ፲፪ ፡ ፩-፰ ታዲያ የዘመናችን መናፍስት ተሞይዎች መንፈስን ተሞ ሩን በሚል ሰበብ አዛንተዛ (የልጆች ጨዋታ)ይጫ ወታሉ ።

መንፈስ ቅዱስን እንደሆነ ዘኢይክል ዓለም ነሥኦቶ ይለዋልምንማለት ነው ቢባል ዓለማዊ ሰውነት ማደሪ ያውሊሆን አይችልም ማለት ነው ፊት ለፊት ወይም

የሸረሪት ድር ከነፋስ ፊት መቆም መቆየት እንዳይ ቻለው ሁሉ ነው ታዲያ ዓለማዊ ሰው ዓለማዊ መሆ ኑን ለራሱ አያቅም ማለት ነው ? ወይስ ማንን ለማ ታለል ነው ? እንዲያውም የሚያስጎዝፍና የሚያን ደፋድፍ መንፈስ ሌላው መንፈስ ነው (ርኩሱ) ፫ኛ በንጽሐ ልቦና ደረጃ ለማንም ያልተገለጸውን የጌታ ስም አውቆ ማመስገን ነው ለምሣሌ እንደ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ራዕይ ፲፱ ፡ ፲፩-፲፯ ።

ራዕይን ብንመለከት በዚህ ዓይነት ነው የሚ ገለጸው በመጀመሪያ በዓለመ ሥጋ ያለውን ከአድ ማስ እስከ አድማስ ያለውን ማየት በዓይነ ሥጋ ሳይ ሆን በዓይነ መንፈስ መርምሮ ማወቅ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፬-፲፮ ።

ቀጥሎም መላእክትን ዓለመ መላእክትን ማየት ከዚያ መድረስ ለምሳሌ ከላይ እንደተጠቀሰው እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ፫ኛ ከነጽሮተ ሥሉስ ቅዱስ መድ ረስ (በቅቶ ሥላሴን ማየት) ለምሳሌ እንደነእስጢ ፋኖስ ቀዳሚ ሰማዕት የሐ ፡ ፯ ፡ ፶፩ ። ማቴ ፡ ፭ ፡ ፰ ይኸንን ሁሉ ደረጃ አልፎ ግን የረቂቃን ረቂቅ የሆነው ጌታን አየሁት ማለት ምን ማለት ነው ? እንዲህ ካለ ሐሰተኛ ቃል ያድነን ። ስለዚህ ቋንቋ መናገርም ሆነ ምሥጢር መተርጐምም የሚቻለው

ከላይ በተነገረው ቃል መሠረት ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ሲሰጥ እንጂ እንዲሁ በፈጠራ ቃል ቋንቋ መናገርም ሆነ መተርጎም የማይቻል መሆኑን ሁላ ችንም ልንገነዘበው ይገባል ።

ሐዋርያትም ቢሆኑ ከላይ እንደጠቀስነው አ ዲስ ቋንቋ የተገለጸላቸው መሆኑን ያረጋገጡት የእ ያንዳንዱን ብሔረሰብ ቋንቋ በመናገር እንጂ አዛ ንትዛ (የልጆች ጨዋታ) በመጫወት አይደለምና።

ይህንንም መንፈስ ቅዱስ የወረደበትን ዕለት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በዐለ ጰራ ቅሊጦስ ብላ በታላቅ ደስታ ታከብረዋለች ቅዱስ ጳውሎስም ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ የዚህን በዐል ታላቅነት ሲያስተምር በኤፌሶን ግን እስከ በዓለ ሃምሳ ድረስ እስነብታለሁ ብሏል በዐ ሉም በዐለ ጰንጠቆስጤ በመባል የታወቀ ታላቅ በዐል ሆኖ ይከበራል ።

መንፈስ ቅዱስ የወረደስት ዕለት ማለት ነው በብሉይ ኪዳን በዓለ ናይት (በዓለ ፋሲካ ማለት ነው) በዓለ መጸለት በዓለ ሰዊት የሚባሉ በዓላት ነበሩ ። ዛሬ በሐዲስ ኪዳን ግን በበዓለ ናይት (በዓለ ፋሲካ) ፋንታ በዓለ ትንሣኤ በበዓለ መጸለት ፋንታ በዓለ አስተርእዩ በበዓለ ሰዊት ፋንታ በዓለ ጰራ ቅሊጦስ ተተክተዋል ።

ስለዚህ ይኸ በዓል እግዚአብሐር መንፈስ ቅዱስ የወረደበት ዕለት በመሆኑ ሁላችንም እንደ ተለመደው ልናከብረው ይገባል ።

መልእክ ሰላምን /ኢየሱስ

# እባብ ተሸክመው የኖሩት ሴት

እባብ ተሸክመው የኖሩ ሴት ስንል አሰቃቂ እንደሚሆን ይሰማናል ሊሆንም የሚገባው ነው አሁን ያለንበት ወቅት ይህን ሁሉ የምንሰማበት የእግዚአብሐርን ድንቅ ሥራ በጠነከረ መልክ የምናይበት ነውና ከዚህ የበለጠም አስደንጋጭ ዜና ልንሰማ እንችላለን ።

ከዚህ ሌላ በዚሁ በ፳ኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ ከዚህ በፊት ያልሆነና ከዚህ በኋላም ይሆናል ተብሎ የማይታሰብ አሰቃቂና ገና በዜናው ሰዎችን የሚ ያስፈራራ መከራ አዘል ዜና ስንሰማ በዓይናችንም እንድናይ ወቅቱ ያስገድደናል ።

ይህን ሁሉ የሚያሰቅቅ ዜና በጆሮ ስንሰማና ደስታ አዘሉንም ታሪክ በተመሳሳይ ሁኔታ ስና ዳምጥ ደስታውና ኀዘኑ በፊታችን ይደቀናል ሆኖም ግን አሰቃቂው ሁኔታ ጎልቶ ሲገጥመን እንደነግጣ ለን እንሸበራለንም መልካም ዕድል ሲያጋጥመን ደግሞ ለደስታችን ወሰን አይኖርለትም ነገር ግን «ይህ ሁሉ የምጥ ጣዕር መጀመሪያ ነው» እንደተ ባለው ደስታው ከዳር የማይደርስ ነው መከራውም ወዲያውኑ የሚያጣድፍ አይደለም ብሎ የራስን መላምት ከመምታት ይልቅ ወይም ከመጠራጠር ተዘጋጅቶና በንስሐ ተመልሶ የጌታን መምጣት መጠባበቅ መልካም ይሆናል ለ፳ ዓመታት በሆዳ ቸው እባብ ተሸክመው ወይም እንደ ልጅ አርግዘው የኖሩት ሴት ማናቸው ? ብለን ብንጠይቅና መልሱን ብናገኝ የእግዚአብሐርን ድንቅ ሥራ እንድንናገር ያስችለናል ።

በመጠይቁ መሠረት መልሱ እባብን በሆዳቸው ተሸክመው የኖሩት ወ/ሮ እቴነሽ ገብረ ሥላሴ የክር ስትና ስማቸው ወለተ ጻድቅ ይባላል እኒህ ሴት አድ ራሻቸው በምሥራቅ ሸዋ ናዝሬት ከተማ ከፍተኛ ፫ ቀበሌ 02 በቤት ቁ - 402 ነዋሪ ናቸው ።

ወ/ሮ እቴነሽ ገ/ሥላሴ ለ፳ ዓመታት በሆዳቸው የኖረው እባብ ሦስት ክንድ ተኩል ሆኗል የክብደቱ መመዘኛ ስላልነበረ ክብደቱን ማወቅ አልተቻለም በግምት ግን ሁለት ኪሎ ክብደት ይኖረዋል ተብሎ ታምኗል ወ/ሮ እቴነሽ ከዚህ ሥቃይን ካስከተለባቸው እርግዝና ለመላቀቅ በሳይንስ ህክምና ሞክረዋል በተለያዩ መንገዶችም ፈትነውታል በሁሉም ለውጥ አላገኙም ሥቃዩ እየበረታ በመምጣቱ በተለያዩ የባህል መድሃኒቶችም ሞክረው መፍትሔ ባለማግ ኘታቸው ምጡ እየገፋ መጣ እባከህ ተወለድ አሉ እቴነሽ አልወለድም አለ እባብም በዚህ ዓይነትትን ትንቅ ላይ እያሉ እግዚአብሔር ምሕረቱን ሲልክላ ቸው ወ/ሮ ሕይወት አገኘሁ የተባሉ ሴት የመፍትሔ ዜና ይዘው ሊጠይቋቸው ወደ ቤታቸው መጡ ።

የመፍትሔው ዜና ምን ነበር ?

ወ/ሮ ሕይወት አገኘሁ የመፍትሔውን ሀሳብ ሲጀምሩ በአሁኑ ሰዓት ያልታመመ ሰው የለም የለበሽታውም መድሃኒት አገኘሁ የሚለው ሰው

በጣት የሚቆጠር እንደሆነ እናውቃለን ወ/ሮ እቴ ነሽም ይሰቃዩ ነበርና ምን ሊሉኝ ነው ብለው በጉጉት ይጠብቁ ነበር አሁን ለርስዎ የምነግርዎ ይህን ሥቃይ በሆድዎ እንዳያዙት ቢሞቱ ለቤተሰብዎ ለወዳጅ ዘመድዎ ሁሉ የማይረሳ ፀፀት ነው ስለዚህ ለሰው ሁሉ መድሃኒት እንዲሆኑ ወደዚህ ዓለም እግዚአብ ሔር ከላካቸው ቅዱሳን አንዱ ቅዱስ ዮሐንስ ነው ቅዱስ ዮሐንስ በሕይወቱ ሥጋ እያለ ሰው ሁሉ ከኃ ጢአት እንዲርቅ ኃጢአት ያለበትም በንስሐ እን ዲመለስ ያስተማረ አባት ነው በአሁኑም ሰዓት ይህ ይቀረዋል የማይባል በሰዎች ላይ ያደረወን በሽታ ሁሉ እየፈወሰው ይገኛል በማለት በሰፊው አብራ ሩላቸው ።

ወ/ሮ እቴነሽም ነገሩ እየጣማቸው ስለመጣ ለመሆኑ ቅዱስ ዮሐንስ ወዴት ነው? እራሱ ዮሐ ንስ ነው? ወይስ ጠበል ነው? ሲሉ ጠየቋቸው ወ/ሮ ሕይወትም መለስ አድርገው ቸኮል ብለው ጠየቁኝ እንጂ በቅዱስ ዮሐንስ ስም በሸንኮራ ወረዳ የፈለ ቀው ጠበል ነው በሽተኞችን ሁሉ የሚያድነው እስካሁን አልሰሙትም መሰለኝ እንጂ የሸንኮራው መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ ጠበል በናዝሬት ከተማ አቶ አሰፋ ወልደ ትንሣኤ በማጅራታቸው ላይ ያበ ጠው እባጭ በሐኪም እንደ ማይድን ሲነገራቸው ከባለቤታቸው ወ/ሮ በላይነሽ ርእሶም ጋር ወደ ጠበሉ በሔዱ በ፫ኛው ቀን እንደ ልጅ ተወልዶ በሽ ታው ወጥቶላቸዋል አቶ አበበ አደራ የተባሉትም ከከባድ የነቀርሳ በሽታ በዚሁ ጠበል ድነዋል በና ዝሬት የዳኑትን ሰዎች እንዘርዝር ብንል ነገሩ ይረዝ ምብናል በጠቅላላው ግን ይህ ጠበል የማህፀንን እና የጡት ካንሰርን ኪንታሮትን በሆድ ውስጥ ያለ የር ስዎን ዓይነት በሽታ በተለይ ለ፲፮ ወራት በሆዷ ተሸ ክማ እያማጠች እያለች ሐኪም የደረቀ ደም (የዕጢ) በሽታ ነው ሲላት ፡ ይህ ጠበል ግን እጥብጥብ አድ እጎ ልጅ ሆኖ እንዲወለድ አድርጋ ለ፳፫ ዓመታት በአልጋ ላይ ተኝተው ይሰቃዩ የነበሩ ወ/ሮ ብሬ ነ እግዚአብሔር እና ሌሎችም በዚሁ ጠበል ድነ ዋል እርስዎም ወደዚህ ጠበል በመሔድ ይዳኑ አሏ ቸው ወ/ሮ እቴነሽ ገ/ሥላሴ ያለምንም ጥርጥር በእ ምነት ተመሥርተው ያለምንም ዝግጅት ወደ ሸን ኮራ ተጓዙ» በዚያም እንባቸውን እያፈሰሱ ጠበ ሉን በጀመሩ በ፯ኛው ዕለት ፫ ክንድ ተኩል የሆነ እባብ መሰል አውሬ ከሆዳቸው ወጣ ወዲያውኑ እፎይ አሉ ድክሚቸውም ተኙ ጠበልተኛ ሁሉ አደነቀ እግዚአብሔርንም አደነቀ ቅዱስ ዮሐንስንም የዘመናችን መንፈሳዊ ሐኪም ለዘለዓለም ስምህ ከጽንፍ እስከፅንፍ ይንገሥ እያለ በእልልታ በጭ ብጨባ ደስታውን አስተጋባ ወዲያውኑ እባቡን በእጃቸው አንጠልጥለው ባለካሜራው አሸብር ወይም ተክለ ዮሐንስ አባተ በካሜራ ቀረጸቸው እንግዲህ የእግዚአብሔር ን ድንቅ ሥራ አጉልተን እንድንና



www.ethiopianorthodox.org

ገር ሳበቃን ለአምላክ ቅዱስ ዮሐንስ ምሥጋና እና ቀርባለን ብሏል ጠበልተኛው ።
እኛም የምንለው የታመማችሁ ሁሉ በእምነት ፀንታችሁ ወደዚህ ጠበል ብትሔዱ ትድናላችሁ እንላለን ።

ሲ- በለጠ አበበ

# ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ የአርሲ ሀገረ ስብከት የልማት ሥራዎችን ጎበኙ ፤

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከሚያዝያ ፲፰-፳ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም በአርሲ ሀገረ ስብከት ሐዋርያዊና አባታዊ ጉብኝት አድርገዋል ። በዚህም ጉብኝት ፦

፩/ በመንበረ ጵጵስናው በ131221.26 ወጭ የተሠሩትን ባለ ፲፩ ክፍሎች ዘመናዊ የእንግዳ ማረፊያ ቤቶች ፤

፪/ በደብረ ምጽላል ቅድስት ማርያም በ44294,29 ብር የተሠራውን የሰንበት ት/ ቤት ወጣቶች መሰብሰቢያ አዳራሽ ፣

፫/ በሀገረ ስብከቱ አቅራቢያ ደብር ቅዱስ በተባለው የችግረኞች ሕጻናት መርጃ ማዕከል በ፩ሚሊወን ብር ሊሠራ የታቀደውንና ለ፲፭ ሺህ ሕዝብ የህክምና አገልግሎት በመስጠት ያስተናግዳል የተባለውን ክሊኒክ የመሠረት ድንጋይ አኑረዋል ።

፬/ በገደብ አሳሳ ደብረ ምህረት ቅዱስ ገብርኤል በ፲፮ ሺህ ብር የተሠሩትን የእንግዳ ማረፊያ ቤቶችና አዳራሽ መርቀው ከፍተዋል ።

፭/ በተጠናከረ መልኩ ጠቅላላ እድሳት የተደረገለትንና ለልዩ ልዩ አገልግሎት መስጫ ተጨማሪ ክፍሎች ተሟልተውለት የተዘጋጀውን የሀገረ ስብከቱን ጽ/ቤት ጎብኝተዋል ።

፮/ ለሕዝቡ ሕይወትና መድኀኒት እግዚአብሔር በገለጸው ራእይ በአንዲት መነኩሲት /እማሆይ/ አመልካችነት ጨፋ በተባለው ቀበሌ ገበሬ ማህበር አዲስ የፈለቀውን ተአምራታዊ ጠበል ባርከዋል ።

፯/ በአካባቢው ቀበሌ ገበሬ ማሕበር ፈቃድና ስምምነት በተከበረው ፳፱ ሄክታር መሬትና በማዕከሉ ሊሠራ የታቀደውን የመድኀኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ጅምር (መቃኞ) ተመልክተዋል ።

ከዚህም ሁሉ ጋር ቅዱስነታቸው በበቆጂ ከተማ በደብረ ፀሐይ ቅ/ጊዮርጊስ ፣በገደብ አሳሳ ደ/ ምህረት ቅ/ገብርኤል ፣

- በአርዳኢታ እግዚአብሔር አብ ፣
- በአሰላ ደብረ መድኀኒት መድኃኔ ዓለም ተገኝተው ጸሎተ ኪዳን በማድረስ እየቀደሱ ፣ በማቁረብና መንፈሳዊ ትምህርት በመስጠት ሕዝበ ክርስቲያኑን ደስ አሰኝተው በሃይማኖት ፣ አጽናንተዋል ።

ዜናዎች በዝርዝር ፦

- የአርሲ ሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና ቀደምሲል በብፁዕ አቡነ ሉቃስ ብርታትና ጥረት ፣ በስከ እንጨት ከተሰራች አነስተኛ የሊቀ ጳጳሱ መኖሪያ በስተቀር የእንግዳ መቀበያና የተመቻቸ አገልግሎት መስጫ ድርጅት ስላልነበረው የቤተ ክርስቲያንን እንግዶች ሁሉ በየሆቴሉ በመቀበል ችግር እንደ ነበረ ተገልጾአል ። አሁን ግን በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በብፁዕ አቡነ ናትናኤል ብልህ አመራር ሀገረ ስብከቱ ካለው ጠቅላላ ገቢ ረዘም ካሉ ዓመታት ጀምሮ የተወሰነ ገንዘብ እየጠራቀመ እንዲቆይ በማድረግ ፮ የመኝታ ክፍሎች ፩ የእንግዶች ማረፊያ /ሰሎን/ ፩ ዕቃ ቤትና ፫ የገላ መታጠቢያ በድምሩ ፲፩ ክፍሎች ያሉት የተሟላ የእንግዶች መቀበያና ማስተናገጃ ቤት መሥራቱ ትልቅ የሥራ እንቅስቃሴ እንደሆነ ተነግሮአል ። የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤትም ብዙ ግዜ አገልግሎት ሰጥቶ በማርጀቱ ሙሉ እድሳት ተደርጎለታል ፤ ፤ በተጨማሪም ፫ የመጸዳጃ ቤቶችና ፩ የአካል ንጽሕና /ሻወር/ ቤት ተሠርቶለት የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ መሆኑ ታይቷል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትሪያርኩ በመንበረ ጵጵስናው የተሠራውን የእንግዶች ማረፊያና የቅድስት ማርያምን ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤት አዳራሽ መርቀው በከፈቱበት ወቅት ባስተላለፉት አባታዊ መልዕክት ሊቀ ጳጳሱ ብፁዕ አቡነ ናትናኤል በሁለንተናዊ መልኩ ያደረጉት የልማት ፣ ሥራ እንቅስቃሴ የሚያስመሰግን መሆኑን አመልክተው ፣ አንድን የታቀደ ተግባር ከፍጻሜ ሊያደርሰው የሚችለው ጉልበትና የገንዘብ ኃይል ብቻ ሳይሆን ፍላጎት ፣ እምነትና በጎ ፈቃድ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል ። ቅዱስነታቸው መግለጫውን በመቀጠል አበው በበጎ ፈቃድ ተነሳስተው በእ[illegible] ስም ሥራ ሲሠሩ ምእመናን ኩተባ[illegible]

ፈጥሮ ሀብት ያልተነካ ከምችት ያላት ስለሆነች ከተሠራባት ለኑሮ የሚያስፈልገው ሁሉ ይገኝባታል ፣ ሌሎች የሚበልጡን በሥራ ነው ፡ በተፈጥሮ ሀብት ሀገራችን ሌሎች የሌላቸው ሀብት ነው ያላት ። ቤተ ክርስቲያን ለኅብረተሰቡ የምታቀርበው አገልግሎት ፡ የቃል ትምህርት ብቻ ሳይሆን በሥራም ምሳሌ መሆን ይኖርባታል ። አበው እንደዚህ ያለውን አርአያነት ያለውን ሥራ ሲሠሩ ፣ ምእመናን ሊያስተውሉትና ሊከተሉት ይገባል። የስብከተ ወንጌል አዳራሽ በየቦታው ያስፈልጋል፣ ወጣቱን ማሰባሰብና ማስተማር የሚቻለው የተመቻቸ ቦታና ዝግጅት ተሟልቶ ሲገኝ ነው ፣ ከቤተ ክርስቲያን ታላላቅ ተግባራት አንዱ ወጣቱን በሃይማኖትና በስነ ምግባር ትምህርት በማጠናከር የአበውን እምነት ፣ ባህልና ትውፊት ፣ ታሪክና ፣ ኃላፊነት ለመረከብ እንዲበቃ ማድረግ ስለሆነ ፣ ይህን የመሰለው ዝግጅት በሁሉም አህጉረ ስብከት በየአብያተ ክርስቲያናቱ በስፋት መቀጠል ይኖርበታል የዘመኑን ጠላት ከወዳጅ ለይቶ በማይታወቅበት በአሁኑ ጊዜ ሕጻናትንና ወጣቶችን በሃይማኖት ተጠንቅቆ መያዝና መጠበቅ እጅግ አስፈላጊ ነው ። ጸረ ተዋሕዶ ተቀናቃኝ የእምነት ፣ ዘማች በስመ ክርስቶስና በስመ ክርስትና በውስጣችን እየተቀየጡ በመንጋው መካከል ተሰግስገዋል ፡ ይሁን እንጂ ከሥራቸውና ከፍሬአቸው ፡ መለየት ስለሚቻል ሕዝበ ክርስቲያኑ ለልጆቹ ፡ በሚደረገው ዝግጅት ሁሉ በመተባበር የቤተሰቡን አባላት ከስተት መንገድ የመጠበቅ ግዴታና ኃላፊነት አለበት ፣ የተሠራው ሁሉ መልካም ስለሆነ በዚሁ እንቅስቃሴ ቀጥሉ እግዚአብሔር ይርዳችሁ ብለዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትሪያርክ ፡ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

- በብፁዕ አቡነ ናትናኤል የሀገረ ስብከቱ ፣ ሊቀ ጳጳስ ብርታትና ጥረት ከአውሮፓ ማኅበረሰብ ኅብረት በተገኘ አንድ ሚሊዎን ብር በደብር ቅዱስ የችግረኞች ልጆች መረጃ ማዕከል ሊሠራ የታቀደውን ክሊኒክ የመሠረት ድንጋይ አስቀምጠዋል ። ክሊኒኩ ለ፲፭ ሺህ ሕዝብ የጤና አጠባበቅ አገልግሎት ይሰጣል ተብሎ የታመነበት ሲሆን የግንባታው ሥራ እንደተጠናቀቀ የሕጻናት መርጃ ማዕከሉ አሁን ከሚረዳቸው ፩፻፳፭ ልጆች በተጨማሪ ቁጥሩን ወደ ፬፻ ከፍ ፣ እንደሚያደርሰው ደረጃም በደረጃም የወንዶችና የሴቶች ሆስቴል ፣ የእንግዳ ቤት ፣ ቤተ ክርስቲያን ፣ እንደሚሠራና የመንገድ ፣ የውሀና የመብራት አገልግሎቶችን ፣ ሁሉ የሚያሟላ ፕሮጀክት እንዳለው ታውቋል ። የአምቦላንስ አገልግሎትም ይኖረዋል ።

ከመንበረ ጵጵስናው ጉብኝት የቀጠለው ከአሰላ ፩፻፲፭ ኪሎ ሜትር ላይ ከሚገኘው የበቆጂ ከተማ ሳይደርስ በግምት ከ፲-፲፭ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ጨፋ በተባለው ቦታ አዲስ የፈለቀው ፈዋሲ ዱያን የጠበል ቦታ ነበር ። ይህ ጠበል የተገኘው ' 'በዚህ ቦታ ምሕረት ወረደ ፣ ለሰው ልጅ ሁሉ ፍጹም ፈውስና ጤንነት ተሰጠ የወርቅ ሚዛን ከሰማይ ወረደ፣ - - - ብለሽ ለህዝብ ንገሪ ፣ እንቺም አድነኝና ልናገር እያልሽ ከዚህ ምንጭ ተጠመቂ ትድኛለሽ - - የሚል ራእይ ደጋግሞ በተገለጠላቸውና በአካልም በአንድ ሕጻን ልጅ አምሳል በተነገራቸው በብርድ ሕመም ይሠቃዩ በነበሩ አንዲት ደካማ መበለት እማሆይ ሣህለ ጊዮርጊስ /የሽዋሐረግ ዓለሙ/ አማካይነት ነው ። ቦታውም ይህን የመሰለ የፈውስና የተአምራት ሥራ ይሠራበታል ተብሎ የማይገመት አልባሌ የእንስሳት መዋያ የነበረ ነው ።

የእግዚአብሐር ሥራ ግን በቦታ ፣ በሰውና ፡ በጊዜ የማይወሰን ሰፊ ስለሆነ ይህን ቦታ በቅዱስ መንፈሱ መርጦታል ፣ ባርኮታል ፡ በተለያየ በሽታ የሚሰቃዩ ወገኖች ከጭንቀታቸው እየተላቀቁ ሙሉ ጤንነታቸውን የሚያገኙበት የፈውስ ማዕከል ፡ አድርጎታል ። የአካባቢው ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ፡ ከእግዚአብሐር የተገኘውን በጎ ስጦታ በማድነቅ ወዶ በመስጠት በከለለው ፳፱ ሄክታር /፪፻፺ ሺህ ሜ/ ካሬ ማዕከል የመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራ ተፈቅዶ ታቦተ መድኃኔ ዓለም በመቃኞ የገባ ሲሆን ብፁዕ አቡነ ናትናኤል ደጋግመው ፡ በመሄድ የቦታውን ቅድስና ለማስከበር ፡ የጠበሉን አካባቢና የተጠማቂዎችን ማረፊያ ሥፍራ በማመቻቸት ሲያጠናክሩ መቆየታቸው » ታውቋል ።

በአሁኑ ጊዜ በሺህ የሚቆጠሩ ሕሙማን ፡ ከተለያየ አቅጣጫ እየመጡ ጠበሉን በመጠጣትና በመጠመቅ ፦

- የተለያየ የሆድ ውስጥ በሽታ
- ቁርጥማትና የሚያለምጥ ሕመም
- የብርድ በሽታ
- የሚያመነምን ደዌ
- የልብ መታወክ ችግር
- የአእምሮ መሳትና የሚጥል በሽታ
- የራስ ፣ የዐይንና የጆሮ ሕመም ችግር



www.ethiopianorthodox.org

የነበረባቸው ጤንነት እያገኙ ወደ የመጡበት በደስታ መመለሳቸውና አሁንም ብዙዎች በጊዜያዊ መጠለያ በደጅ ጥናት ላይ የሚገኙ መሆናቸው ታውቋል ። ጠበሉ በተጠቀሱት እማሆይ አመካኝነትና በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ገና በብዙ ቅዱሳን ስም ምልክት እየተደረገለት ያለ በብዙ ቦታ ላይ የሚፈስ ሲሆን አሁን በሥራ ላይ ያሉት የመድኃኔዓለም ፣ የእግዚአብሔር አብ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ጠበሎች ናቸው ። የጠበሉ ቦታ ቀደም ብሎ ግንቦት ፲፪ ቀን ፲፱፻፹፮ ዓ/ም በቀሳውስት ተባርኮ የተአምራት ሥራውን በመቀጠል ያለ አጥማቂ ካህን በሽተኞች እየጮሁ ከሕመማቸው ሲገላገሉ መቆየታቸው ቢታወቅም ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩና ሌሎች ፭ ሊቃነ ጳጳሳት አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ወቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ብለው ባርከውታል ። ጠበሉን ለተጠማቂዎች በሚያመች መልኩ ለማደራጀት የክፍሉ የቀይ መስቀል ማኅበር በዝግጅት ላይ እንደሆነ ተገልጾአል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ጠበሉን በባረኩበት ወቅት በእምነት ለሚከታተለውና ለሚያስተውለው ሁሉ የእግዚአብሔር ሥራ ዕለት ዕለት የማይቋረጥ የኃይልና የተአምራት ሥራዎቹም ዘወትር የሚታዩ መሆናቸውን ጠቁመው ጠበል ለኛ ለኢትዮጵያውያን አዲስ አለመሆኑን ፣ በእምነት መሣሪያነት የምንድንበትና የምንፈወስበት ህክምናችን ሆኖ መኖሩን ገልጸዋል ። በማስተዋል ፣ በትዕግስትና በእምነት ከተራመድን ፣ የኛ የምንለውን እምነታችንን ካላቃለልነው ብዙ ድንቅ ሥራዎችን እናያለን ፣ ጥርጥርም ካላስገባንበት የምንሻውን ሁሉ ልናገኝ እንችላለን ፣ የኢትዮጵያ ምድር አየሩም ውሀውም አፈሩም ዕጸዋቱም ሁሉ የተቀደሰ ስለሆነ ሕይወት መድኃኒት ነው ብለዋል ።

የጪፋ መድኃኔ ዓለም ጠበል ታሪክና ዜና በለብለብ የሚታለፍ ስላልሆነ ለጊዜው ይህን ብለን በሌላ ጊዜ ሠፋ አድርገን እንመለስበታለን ።

ከዚህ በኋላ ጉብኝቱ የቀጠለው ወደገደብ አሳሳ ነው ።

ገደብ አሳሳ ከበቆጂ ቀጥለው ከሚገኙት ከተሞች ሞቅ ደመቅና ጎላ ያለው ከተማ ነው ። ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩና ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በከተማው ገብተው በደብረ ምህረት ቅ/ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ግቢ የተሠራውን የእንግዳ ማረፊያ ቤት መርቀዋል ፣ የሰበካ ጉባኤውን ሁለንተናዊ የልማት እንቅስቃሴ ተመልክተዋል ፣ በዚሁ የአሳሳው ደብረ ምህረት ቅ/ገብርኤል ሰበካ ጉባኤ ፣ ጽ ቤት

- ብፁዓን አበውና የቤተ ክርስቲያን ታላላቅ እንግዶች የሚያርፉባቸው የአካል መታጠቢያ ቤቶችና የእንግዳ መቀበያ ክፍል (ሳሎን) ያላቸው ዘመናዊ የመኝታ ክፍሎች በብር 28751.65 ወጭ አሠርቷል ።

- 17.625.77 ሜትር ካሬ ስፋት ያለውን አፀደ ቤተ ክርስቲያን በ2.5 ሜትር ከፍታ የግንብ አጥር አሳጥሮአል ፣ ለሕጥሩ ግንባታ በገንዘብ የወጣው ብር 80,000 ሲሆን ሕዝቡ በጉልበቱና በዕውቀቱ ያደረገው አስተዋጽኦ ብር 20,000 ተደምሮበት ሥራው በ፲፱፻፹፯ ተጀምሮ በዚህ ዓመት መጠናቀቁ ታውቋል ። ለቤተ ክርስቲያኑ መንፈሳዊ አገልግሎት አስፈላጊ የሆነው የውሃ ቧንቧ በብር 2.000 ተሠርቷል ፣ በአጥቢያው ምእመናን ተደረገ የነፍስ ወከፍ አስተዋጽኦና ከአንድ በጎ አድራጊ ግለሰብ በተገኘ ብር 4,000 በድምሩ 17,000 የድምፅ ማጉያ ተገዝቶ ሥራ ላይ ውሏል ፣ በአፀደ ቤተ ክርስቲያኑ የአጸድ ዛፍ ተከላ ተከናውኖአል ። በዚህ ሁሉ የልማት ሥራ እንቅስቃሴና ውጤት ሰበካ ጉባኤውንና ምእመናንን በትጋት አስተባብረዋል የተባሉት መምህር ተስፋ ኪሮስ የመልአከ ምህረት የማዕረግ ሥያሜ አግኝተዋል ። ሚያዝያ ፲፱ ቀን ፲፱፻፹፰ ዕለተ ቀዳሚት በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ መሪነት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በዚሁ ደብር ቀድሰው አቁርበዋል ። ሠፊ ትምህርትና መመሪያም ሰጥተዋል ። ከዚህ ሁሉ በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ጳውሎስና ብጹዓን ሊቃነ ጳጳሳት ሐዋርያዊ ጉዞአቸውን ወደምሥራቃዊ አርሲ በመቀጠል በአርዳኢታ እግዚአብሔር አብ ጸሎተ ኪዳን አድርሰው ከአካባቢው ለተሰበሰበው ሕዝብ በየካቲት ፳፰ የግብርና ሙያ ምርምርና ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት አዳራሽ ትምህርት ሰጥተዋል ።

በፍጻሜው ወደአሰላ ተመልሰው እሑድ ፣ ሚያዝያ ፳ ቀን ፲፱፻፹፰ በመድኃኔ ዓለም ቤተ፡ክርስቲያን በመገኘት ቀድሰው አቁርበዋል ፣ ብፁዕ አቡነ ቶማስ ፣ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ በየተራ ለሕዝቡ ትምህርት ሰጥተው ጠቅላላ ጉብኝቱ በብፁዕ ወቅዱስ ፓትሪያርክ ጸሎትና ቃለ በረከት ተጠናቋል ።

ጉብኝቱ በዚሁ ተጠቃሎ ወደ አዲስ አበባ መልስ በሆነበት ጊዜ የተጎበኘው በሑሩታ ፈጠስ በብር 100,000 የአርሲ ሀገረ ስብከት ከአካባቢው ቀበሌ ገበሬ ማኅበር የገዛው አጸደ ሕጻናት ቤትና ቦታ ነው ። ይህ ቤትና ቦታ ከትምህርት ጉዞ በመፈናቀል ለሚቸገሩ ወጣቶች ማሠልጠኛ እንደሚሆን ተገልጾአል ።

በሀገረ ስብከቱ በተደረገው ሐዋርያዊ ጉብኝት በተግባር በታዩት የልማት ሥራዎች ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ የሀገሩ ስብከቱን ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ናትናኤልን አመስግነዋል ፣ ሌሎችም ሥራውን አብረው የተመለከቱ ብፁዓን አበው መልካም ምሳሌነቱን ለራሳቸውና ለሌሎችም አበው እንዲያበሥሩ አባታዊ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል ።

እኛም የዜናዎች ማጠናቀሪያና ማሠራጫ ክፍሎች በሀገረ ስብከቱ ያየነውንና የተመለከት ነውን የልማት እንቅስቃሴ የሚጣፍጥ ፍሬ መስጠት የጀመረ ስለሆነ የብፁዕ ሊቀ ጳጳሱን ብልህ አመራርና ትጋት ያለው ርምጃ በብዙ አድንቀናል ፣ በሁሉም ማዕዘን ተመሳሳይ ሂደቱ ይቀጥል ብለናል ።

መልአከ ሰላም ዳኛቸው ካሣሁን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ኃላፊ ።



## የሴቶች ዓምድ

አዘጋጅ ወ/ት መአዛ አስማማው

## የሴቶች ምስክርነት

የዓለም ቤዛ የሆነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶ ሰማያዊ ዙፋኑ ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በምድር ላይ ፴፫ ዓመት ከ፫ ወር ተመላልሶ በኃጢአት ረክሶ የነበረውን ዓለም በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ በፈሰሰው ደሙ አነጻው ። ይህንም ያደረገው የሰው ልጅ ፍቅር አገብሮት መሆኑ ግልጽ ነው ።

ስለዚህ የሰው ልጅ ፍቅር ስንል ወንድ ወይም ሴት ሳይሆን ሁለቱንም መሆኑን ለማመን ክርክር መግጠም አያስፈልግም ። የእያንዳንዱ ሕሊና እምኖ ይቀበለዋልና ።

በዘመነ ነቢያት በነበረው የምሥክርነት ጊዜም ረዓብ ያትባለችው ሴት በእምነት ነቢያቱን ተቀብላ « እግዚአብሔር አምላካችሁ በሰማይ ላይ አምላክ ነው ፣ በምድርም በታች» ብላ መስክራ ስላስረዳቻቸው ከሌሎቹ ጋር አልጠፋችም ። (ኢያሱ ፪ ፣ ፲፯)

መድኅኒታችንም ወደዚህ ዓለም መጥቶ በሚያስተምርበት ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ ተለይቶ ከአንዲት ሳምራዊት ጋር ሲነጋገር እርሱ ከሚሰጠው ውሃ የጠጣ ለዘለዓለም እንደማይጠማ ከርሱ የሚገኘውን የሕይወት ምሥጢር ከገለጸላት በኋላ መሢሕ ክርስቶስ እኔ ነኝ ባለት ጊዜ ማድጋዋን ትታ ለሀገርዋ ሰዎች መጥታችሁ እዩ ብላ መስክራ ነበር ።

ሰዎቹ ወደመድኀኒታቸው እየገሠገሱ መጥተው ብዙዎቹ አመኑበት ። ከሚከተሉት ከብዙ ሺ ሕዝቦች መካከልም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ለመንፈሳዊው ተልእኮ ከተጠሩት ፴፮ ሴቶች (ቅዱሳት አንስት) ነበሩ ።

እንደዚሁም በመከራው ሣምንት ከሞተ በኋላ በሦስተኛው ቀን መነሣቱን በነገራቸው ጊዜ ያለምንም ጥርጥር በፍጹም ልቡናቸው አምነው ትንሣኤውን አይተው ለደቀ መዛሙርቱ እንዲነግሩ የተላኩት ሴቶች ነበሩ ። ከሐና ወደቀያፋ ከቀያፋ ወደ ሐና አብረው የተንከራተቱ እስከመስቀልም ድረስ ሳይለዩት ያለቅሱለትና ያዝኑለት የነበሩ እነርሱ ናቸው ።

ልዑል አምላክ ግን የማንንም በጎ ተግባር ዋጋ የማያሳጣ በመሆኑ በሲኦል ላሉት ነፍሳት ሰላምን ሰብኮ ከሙታን ተለይቶ በተነሣ ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ አስቀድሞ ለነርሱ በመታየት ሔደው እንዲመሰክሩላቸው አዝዟቸዋል ።

እንግዲህ የመጀመሪያ የትንሣኤ ምሥራች ነጋሪ መሆን ዋጋ የለውም እንል ይሆን? የምንል ከሆነ ተሳስተናል ። ከእርሱ ጋር መጨነቅና የሕማሙ ተካፋይ ሆኖ በፋሲካውም የደስታው ባለሟሎች መሆንስ እንዲትን ሴት የትንሣኤ መስካሪ ከሚያሰኙት ነገሮች አንዱ አይሆን ይሆን? ሁላችን ሕሊናችንን የመረመረን እንደሆነ ግን ስንቶቻችን ይህ ተረድቶናል? ለወንዶች ብቻ ሰላምን ሰበከ እንዳንል ለኛም የምሥራች ዜና አቅራቢዎች እንድንሆን የቅድሚያ ዕድሉን ችሮናልና ግን ከዚህ ዕድልና ደረጃ ከደረስን በጾታችን ምክንያት በክርስትና ሕይወታችን ምንም ልዩነት እንደሌለ በማመን ሕይወትና ትንሣኤ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን በማይቋረጥ ምስክርነት መግለጥ አበው ላቆዩልን እምነትና ትውፊት በተግባር ማሳየት ይኖርብናል ።

## ልደታ ለማርያም

ከዓለም መፈጠር በፊት አስቀድሞ በሕሊና ሥላሴ ታስባ ትኖር ስለነበረችውና በኋላም ሥግው ቃል ወልደ እግዚአብሔርን ስለወለደችው ስለቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ልደት በመንፈስ ቅዱስ እየተቃኙ በልዩ ልዩ ትንቢትና ምሳሌ አበው ነቢያት መናገራቸውን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዱናል ።

ትወጽእ በትር እምሥርወ እሴይ
ወየአርግ ጽጌ እምጉንዱ ኢሳ ምዕ ፲፩-፩-፫

ከእሴይ ግንድ ሥር በትር ትወጣለች ከሥሩም ቁጥቋጦ ያፈራል በማለት ነቢዩ ኢሳይያስ የተናገረው ለጊዜው የትውልደ እሴይን ተከታታይ ሥልጣን ቢሆንም ፍጻሜው ግን ስለቅድስት እመቤታችን ድንግል ማርያም መወለድ ነው እንዲሁም ነቢዩ ሙሴ ነበልባሉ ሐመልማሉን ሳያቃጥለው ሐመልማሉ ነበልባሉን ሳያጠፋው በሲና ተራራ ላይ ተመልክቷል ዘጸ ፫-፪-፭ ይኸውም ነበልባሉ የወልደ እግዚአብሔር ሐመልማሉ የእመቤታችን ምሳሌ ነው ።

በካህኑ በአሮን ዘመነ ክህነት በነቢዩ በሙሴ ዘመነ ምስፍና (የአስተዳደር ዘመን) በተንኮልና በምቀኝነት በሙሴና በአሮን ላይ የተነሱት ዳታንና አቢሮን ቆሬ በክፉ ሥራቸው ከጠፉ በኋላ እግዚአብሔር ሙሴን በአዘዘው መሠረት ከአሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል አሥራሁለት በትሮች ወስዶ የእያንዳንዱን ነገድ ስም በየበትሩ ጫፍ ጽፎ በመገኛው ድንኳን በምስክሩ ታቦት ፊት አስቀምጦ ካደረ በኋላ ከሌዊ ነገድ የሆነው የአሮን በትር አብባ ለምልማ አፍርታ ተገኝታ ነበር ።



www.ethiopianorthodox.org

ይኸውም ለጊዜው ቅብዐ ክህነት ከሌዊ ቤት እንዳይወጣ እግዚአብሔር የፈቀደ መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን ፍጻሜው ግን ያች የለምለመችው በትር የወልደ እግዚአብሔር እናት የሆነችው የእመቤታችን ድንግል ማርያም የመገኘቷ ምሳሌ ናት ዘኁልቍ ፲፯-፩-፲፩ ስለዚህም ነው ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም «በትር አሮን አንተ ሠረጸት ዘእንበለ ተክል ወኢሠቀይዋ ማየ ከማሃ አንቲኒ እ ወላዲተ ክርስቶስ» የክርስቶስ እናቱ ሆይ ውሃ ሳያጠጧት አብባ ለምልማ አፍርታ የተገኘችው የአሮን በትር ምሳሌ አንች ነሽ በማለት በውዳሴ የገለጸው ።

ከዚህም ሌላ እመቤታችን ከኢያቄምና ከሐና ከመወለዷ በፊት በብሉይ ኪዳን ዘመን በኖህ መርከብ በሴም በረከት ሥላሴ በእንግድነት በገቡባት በአብርሃም ድንኳን ከምድር እስከ ሰማይ ተተክላ መላዕክት ሲወጡባት ሲወርዱባት ያዕቆብ ባያት በብርሃን መሰላል ከሰማይ ጠል በወረደባት በጌዴዎን ጸምር በሙሴ ታቦት እየተመሰለችና እየተገለጸች በአበው ነቢያት ትንቢት ትነገር ነበር ።

ለሰው ልጅ የተሰጠው የሕይወት ተስፋ ጊዜው ሲደርስ (ሲቃረብ) ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም በፈቃደ እግዚአብሔር በሕገ እግዚአብሔር ጸንተው ከኖሩት ከኢያቄምና ከሐና በብሥራተ መልአክ ተጸንሳለች «አኮ በፍትወት ደነስ ዘተጸነሥኪ እላ በሩካቤ ዘበሕግ እምሐና ወኢያቄም ተወለድኪ » በፍትወት በደነስ የተጸነስሽ አይደለሽም በሕገ እግዚአብሔር ጸንተው ከኖሩት ከኢያቄምና ከሐና ተወለድሽ እንጅ በማለት ሊቁ አባ ሕርያቆስ የተናገረው ስለዚህ ነው ።

የቅድስት ድንግል ማርያም ወላጆች እንደ ቀድሞ ኢያቄ(ም) መሆኖች ነበሩ ይህንም የመሆ(ን)ነት ችግር እግዚአብሔር እንዲያስወግድላቸውና ልጅ እንዲሰጣቸው ዘወትር ይጸልዩ ነበር «ወርዕየ እግዚአብሔር ላዕለ ሐሊናሆሙ ወሠናይ ሐሪቶሙ ወሰምረ [illegible] [illegible] ይኩን [illegible] [illegible] [illegible] [illegible] እግዚአብሔር አምላክም [illegible] [illegible] ሰማይ [illegible] [illegible] [illegible] [illegible] [illegible] እንዲሁም [illegible] [illegible] ማህጸን [illegible] ከቤታቸው አጠገብ አንዲት ዛፍ ለምልማ አብባ አፍርታ ሰው ሁሉ ሲመገባት እንዲሁም ለኢያቄም የክብር ዘንግ የብርሃን መነሳንስ ሲእሲዙት በሕልም ጌታ ከገለጸላቸው በኋላ የዓለሙ ሁሉ የሕይወት መሠረት የሆነችው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በብሥራተ መልአክ ነሐሴ ፯ ቀን ተጸንሳ ግንቦት ፩ ቀን ተወለደች ።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በቅድስተ ሐና ማህጸን በነበረች ጊዜ ልዩ ልዩ ተአምራት አድርጋለች ይኸውም እንዲት አንድ ዐይና ሴት የሐናን ጡት ነክታ የጠፋውን ዐይኗን ብትነካው በር የሐናን ቶላታል እንዲሁም አንድ ሳምናስ የተባለ የሐና የአጎቷ ልጅ ሙቶ ሳለ ሐና በጣም ትወደው ስለነበር በአስከሬኑ አጠገብ እየተመላለሰች ስታለቅስ ያ የሞተው ሰው ብድግ ብሎ «ኦ ሐና እማ ለጸሐየ ጽድቅ ወእምሄቱ ለዘገብረ ሰማየ ወምድረ»

ሐና ሆይ ጸሐየ ጽድቅ የተባለች የእመቤታችን ድ/ማርያም እናት ሰማይ ምድሩን ለፈጠረው ጌታ አያት አንች ነሽ በማለት ቀድሞ ከመፈክረ ሕልም የተሰወረውን ተርጉሞ ተናግሯል እመቤታችን ቅድስት ማርያም በሐና በእናቷ ማህጸን ሁና እነዚህንና ሌሎችንም ተአምራት ስለፈጸመች አይሁድ ተመቅኝተው የዚህች ቅድመ እያቶች እነ ዳዊት እነ ሰሎሞን አርባ ዓርባ ዘመን ገዙን ከዚህች የሚወለደውማ ገና በእናቱ ማሕጸን እያለ እንዲህ ያደረገ በኋላማ እንዴት ይሆን ብለው ሐናን ሲጣሏት ስለአሰቡ ኢያቄም ሐናን ይዞ ወደተራራማው አገር ሂዷል ።

«መሠረታቲሃ ውስተ አድባር ቅዱሳን ያበድሮን እግዚአብሔር ለአናቅጸ ጽዮን እምኩሉ ተአይኒሁ ለያዕቆብ » መሠረቶቸ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው ከያዕቆብ ድንኳኖች ይልቅ እግዚአብሔር የጽዮንን ደጆች ይወዳቸዋል የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ በአንች የተከበረ ነገር ይባላል መዝ ፹፯ ቁ ፩-፬ እያለ ነቢዩ ዳዊት በመዝሙር በገለጸው ትንቢት መሠረት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በተራራማው አገር ግንቦት አንድ ቀን ተወልዳለች ።

ስለዚህም ነበር ኢትዮጵያዊ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ «እምሊባኖስ ትወጽእ መርዓት ወትወጽኢ እምግበበ አናብስተ ወእምታዕካ ዘነገሥት » መርዓት የተባለች ድንግል ማርያም ሊባኖስ ከተባለው ተራራማ አገር ትወጣለች እንዲሁም ከአንበሶች ጉድጓድ ከነገሥታቱ ከዳዊት ከሰሎሞን አደራሽ (ከዳዊት ዘር) ትወጣለች እያለ በጣዕመ ዝማሬው ያወሳው ።

በኃጢአት መርገም ተይዞ በመንጸፈ ደይን ወድቆ ከፈጣሪው ተጣልቶ ይኖር ለነበረው የሰው ልጅ ውርደቱ በክብር ሐጢአቱ በጽድቅ ሞቱ በሕይወት ተተክቶ ከፈጣሪው እንዲታረቅ መሠረት የተጣለበት የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም የልደት ቀን ነው ።

ለእመቤታችን ከልጅዋ ከፈጣሪዋ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጣትን ቃል ኪዳን በማሰብና ረድኤቷ በረከት ለማግኘት የሚወዱ እርትዶክሳውያን ምእመናን በእመቤታችን የልደት ቀን የታረዘ በማልበስ የተራበ በማብላት የተጠማ በማጠጣት የተጣላ በማስታረቅ የእመቤታችን በዐለ ልደት ሲአከብሩ አንዳንድ ሁኔታው ያልገባቸው ግለሰቦች የእመቤታችን በዐለ ልደት በሚውልበት ግንቦት አንድ ቀን ንፍሮ አንፍረው ጥሬ ቆልተው ቂጣ ጋግረው ለተራብ በመስጠት ፈንታ ንፍሮውን ቂጣውን በየመንገዱ እየበተኑ ለሰይጣን ሲገብሩ ይታያሉ ።

በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ይህን ሠይጣናዊ ሥራ የሚፈጽሙ ሰዎች እህል በተወደደበት ርሀብ ተኛ በበዛበት በአሁኑ ጊዜ እህል በየመንገዱ መድፋታቸውንና ለሰይጣን ግብር ማቅረባቸውን እርግፍ አድርገው ትተው ንስሐ ገብተው የሰው ልጅ የሕይወት ውል በተገኘበት በእመቤታችን የልደት

ለተጠማ በማጠጣት ከእመቤታችን ረድኤት በረከት እንዲያገኙ በኋላም የማያልፈውን የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲወርሱ ወንጌላዊ ትምህርታችን እናስተላልፋለን ።

የእመቤታችን ረድኤት ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን

መሪጌታ ኤፍሬም በየነ

---

# ፍልሰተ አጽሙ ለተክለ ሃይማኖት

ብዙ ጻድቃን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሰው ልጅ ድኅነት ሲል በዕለተ ዓርብ ከአይሁድ የተቀበለውን ፀዋትወ መከራ በማሰብ እነርሱም ሥጋቸውን ለልዩ ልዩ ሥቃይና መከራ ሰጥተዋል በዚሁም ብዙ ክብርና ቃል ኪዳን ተቀብለዋል ። ከነዚህም ጻድቃን ውስጥ ታላቁ ኢትዮጵያዊ ጻድቅ አቡነ ተክለሃይማኖት ናቸው ።

አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገድላቸው እንደሚገልጸው የትውልድ ሐረጋቸው ከአዳም እስከ አብርሃም ያለውን ተንትኖ ሲገልጽ ከዚያም ቀጥሎ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር የኦሪትን ሕግና ታቦተ ጽዮንን ይዘው ከኢየሩሳሌም እስከ አክሱም ድረስ ከመጡ ካህናት ከነአዛርያስ አንስቶ እስከ ወላጅ አባታቸው እስከ ፀጋ ዘአብ ያለውን ሐረገ ትውልዳቸውን ዘርዝሮ ያስረዳል ።

በዚህ መሠረት ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ትውልድ ሐረጋቸው ከጻድቃን ከካህናት ወገን መሆናቸውን በቀላሉ ከተረዳን የጻድቁ አባታቸው ፀጋዘአብ እናታቸው እግዚእ ሐረያ ይባላሉ የተወለዱበትም አገር በሸዋ ሀገረ ስብከት በቡልጋ አውራጃ በተለይ ደብረ ጽላልሽ በተባለች ቦታ መሆኑን መጽሐፈ ገድላቸው በጥሩ ሁኔታ ይገልጻል ።

የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አባትና እናታቸው ልጅ አጥተው ልጅ እንዲሰጣቸው ብዙ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልዩ ከቆዩ በኋላ ከዕለታት አንድ ቀን ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት በሕልም መጥቶ አሕዛብን ከአምልኮተ ጣኦት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር የሚመልስ ለዓለም ብርሃን የሚሆን ልጅ ትወልዳላችሁ ብሎ ነገራቸው» በዚሁ በመልአኩ ብሥራት መሠረት ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በ፩ሺ፩፻፺፯ ዓ/ም ታኅሣሥ ፳፬ ቀን ከእናታቸው ከእግዚእ ሐረያ ተወለዱ ።

ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት «ቀደስኩከ እምከርሠ እምከ» ከእናትህ ማኅፀን ጀምሮ መረጥኩህ ተብሎ የተነገረላቸውና ከእናታቸው ማኅፀን ጀምረው የተመረጡ ስለሆኑ ከሕፃንነታቸው ጀምረው በእግዚአብሔር ፀጋና ረድኤት የተሞሉ በመሆናቸው በተወለዱ ጊዜ አሐዱ አብ ቅዱስ ፣ አሐዱ ወልድ ቅዱስ ፤ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ፣ ብለው ፈጣሪያቸውን አመስግነዋል በዚሁ ባሕፃንነታቸው ወራት ሳሉ በሀገራቸው ረሐብ ሆኖ እናታቸው እግዚእ ሐረያ ለቅዱስ ሚካኤል በዓል የሚዘክሩት እህል አጥተው ሲያዝኑና ሲቸገሩ ሕፃን ተክለ ሃይማኖት አይተው ጥቂት በዕንቅብ የነበረ ዱቄትና በ ማሰሮ የነበረ ጥቂት ዘይት እንዲያቀርቡላቸው በእጃቸው አመለከቷቸው በዚህ ጊዜ እናታቸው እግዚእ ሐረያ ይህ ሕፃን ምን ድነው የሚለኝ ? ብለው በዕንቅብ የነበረ ጥቂት ዱቄትና በእንስራ የነበረ ጥቂት ዘይት አቀረቡላቸው በዚህ ጊዜ ሕፃኑ ተክለ ሃይማኖት «በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ብለው አማትበው እጃቸውን ቢያሳርፉበት ጥቂት የነበረ ዱቄትና ዘይት ተትረፍርፎ ፲፪ ዕንቅብና ፲፪ እንሥራ ሞልቶ በዚሁ የቅዱስ ሚካኤልን በዓል አክብረው ችግረኞች ነዳያንና ምስኪናንን አብልተው አጥግበው ደስ አሰኝተዋቸው ውለዋል ።

ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የመጀመሪያ ስማቸው ፍሥሐ ጽዮን ነበር ኋላ ግን ጌታችን ኢየሱስ ተገልጾ ’ ’ አፍቅርየ ተክለ ሃይማኖት አኮኑ አነ ረሰይኩከ ወፈነውኩከ ትስአር ጣኦታት ወትቀድስ ታቦታተ ወትሢም ካህናተ ወዲያቆናተ ወትኩን ብርሃነ ለአሕዛብ በውስተ ዛቲ ብሔረ ጽልመት ’ ’ ወዳጅ ተክለሃይማኖት ሆይ ጣዖታትን ትሽር ዘንድ ካህናትን ትሾም ዘንድ እኔ ሾሜህ ለሁ በማለት ከተናገራቸው በኋላ ከዚያን ጊዜ ጀምረው የወንጌል ትምህርት በኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር እየዞሩ በመስበክና በማስተማር በአምልኮ ጣኦት የነበሩትን ሕዝብ አስተምረው ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር መልሰው አጥምቀው አቁርበው አብያተ ክርስቲያናት ሠርተው ካህናትንና ፣ ዲያቆናትን ሹመው በሃይማኖታቸው እንዲጸኑ ፣ አድርገዋል ።

ከነዚህም ውስጥ በዚያን ጊዜ ዳሞት በአሁኑ ወላይታ ተብሎ ከሚጠራ አገር መተለሜ የተባለ የአገሩ ንጉሥ ልዩ ልዩ ተአምራት እያደረጉ ንጉሡን ከነሠራዊቱ የአገሩን ሕዝብ ጠቅላላ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም አስተምረው ካሳመኑ በኋላ በአገሩ የነበሩትን ጣኦታትን ደምስሰው ማርያን የተባሉትን ጠንቋዮች አጥፍተው አብያተ ክርስቲያናትን ሠርተው ካህናትን ዲያቆናትን ሹመው በሃይማኖታቸው ፀንተው እንዲኖሩ አድርገዋል ። ስለዚህም ’ ’ አማን በአማን ተክለ ሃይማኖት ፀሐይ ’ ’ እየተባሉ በቤተ ክርስቲያን እየተመሰገኑ ይኖራሉ ።

ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በርዕሱ እንደ ተገለጸው ሁሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሰው ልጅ ድኅነት ስለዓለም ቤዛ ሲል ከአይሁድ የተቀበለውን ፀዋትወ መከራ በማስታወስ ሰውነታቸውን የሚወጉ በቀኝ ጐድናቸው በኩል ሦስት የብረት ጦር ፣ በግራ ጐድናቸው በኩል ሦስት የብረት ችንካር ፣ አድርገው በአንድ እግራቸው ቆመው ጥቂት ሽንብራ እየተመገቡ ለ፯ ዓመታት ተጋድለዋል በዚህ ጊዜ ከቋመት ብዛት የተነሣ ቀኝ እግራቸው ተሰብራ ክንፎች አውጥተዋል እንደገናም በአ



www.ethiopianorthodox.org



ጻድቅ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡

ነኑ እግራቸው ቆመው ለ፯ ዓመታት ጸለየዋል ።
በበዚህም ' ' ተክለ ሃይማኖት ያዕቆብ እንተ
እግርከ ገመድ ' ' ያስተበጽእከ በግያውን ነገድ።
አስያገምነሙ እሳተ በእድ ' ' ተብሎ ተደርሶላቸ
ዋል ይህም ማለት እንደያዕቆብ ስግዕት እግርህ
የተቆረጠ ተክለ ሃይማኖት ሆይ እሳትን የሚይዙ
መላእክት ያደንቁሃል ማለት ነው ። የጻድቁ አቡነ
ተክለ ሃይማኖት ክቡር አጽማቸው ለ፶፯ ዓመታት
በጸለዩበት በደብረ አሰቦት ገዳም ተቀምጦ ሲኖር
በ፲፫፻፹፮ ዓ/ም ብዙ መነኮሳት በብዙ ሺህ የሚቆ
ጠሩ ምዕመናንን ተሰብስበው እየዘመሩና እያመ
ሰገኑ ግንቦት ፲፪ ቀን በትልቁ ገዳማቸው በደብረ
ሊባኖስ በክብር ተቀምጧል በዚሁ ክቡር አጽ
ማቸው በተቀመጠበት ቤተ ክርስቲያንም ብዙ ፡
ድውያን በየጊዜው ይፈወሳሉ በዚሁ መሰረት ግን
ቦት ፲፪ ቀን በየዓመቱ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ምዕ
መናን ከየክፍላተ ሀገሩ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይ
ማኖት ክቡር አጽማቸው የፈለሰበትን በዓል ለማ
ክበር በረከታቸውን ለመቀበል ወደ ደብረ ሊባኖስ
ይሄዳሉ በዚህም ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፡
በተቀበሉበት ቃል ኪዳን መሠረት በረከትንና ፡
ረድኤት ተቀብለው ይመለሳሉ ።

የጻድቁ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት
በረከትና ረድኤት በሕዝበ ክርስቲያ
ንላይ ለዘለዓለም ይኑር አሜን
መ/ ምሕረት ብርሃኑ ተስፋየ

www.ethiopianorthodox.org